# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

## POVERTY DIALOGUE FORUM

*Consultation Papers on Poverty No. 4*



# የ ድ ሆ ች ድ ም ፅ
# Listening to the Poor


*Edited by*
*Meheret Ayenew*



**Addis Ababa**
**November 2001**

# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

## POVERTY DIALOGUE FORUM

*Consultation Papers on Poverty No. 4*

# የ ድ ሆ ች ድ ም ፅ
# Listening to the Poor

***Edited by***
***Meheret Ayenew***

**Addis Ababa**
**November 2001**

**The opinions expressed in this publication are those of the authors and do not necessarily reflect the views of FSS or its Board of Advisors.**

# ማ ው ጫ


መግቢያ……………………………………………………………………………………. 1
ምህረት አየነው
የፕሮግራሙ አቀነባባሪ

Summary of Presentation………………………………………………………….. 2

የውይይቱ አቅራቢዎች ከመድረክ…..…………………………………………………….. 5

ተጨማሪ ውይይት አቅራቢዎች...………………………………………………………… 11

አጠቃላይ ውይይት...………………………………………………………………… 13

# መ ግ ቢ ያ

በአገራችን በኢትዮጵያ የሚታየው የድህነት መጠንና ስፋት በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ከችግሩ ስፋትና አንገብጋቢነት አንፃር መንግሥት ብቻውን ሊወጣው አይችልም፡፡ ስለዚህ ችግሩን ለመቅረፍ መንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ፣ ዕርዳታ ለጋሽ መንግስታትና ድርጅቶች መረባረብ ይኖርባቸዋል፡፡ አገራችን በልማት ወደፊት እስካልተጓዘች ድረስ የድህነት ችግር እየባሰበት እንደሚሄድ ግልጽ ነው፡፡

አገራችን ውስጥ ተንሰራፍቶ ስለሚታየው የድህነት መጠንና ይህንን ችግር ለመቅረፍ መደረግ ስላለበት ጥረት **የማኅበራዊ ጥናት መድረክ /ማጥመ/** የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ ውይይት ሲያደርግ የዛሬው አራተኛው ነው፡፡ ማጥመ ይኽ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ መድረክ የከፈተው ስለድህነት ችግርና መፍትሔ የችግሩ ሰለባ የሆኑ ወገኖች ተሳታፊ መሆን አለባቸው ብሎ ስለሚያምን ነው፡፡

የዚህ የአራተኛው ውይይት ተሳታፊዎች ከድሃው ሕብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ናቸው፡፡ ከእነሱም መካከል ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ ለከፍተኛ ድህነት የተጋለጠውን የሕብረተሰብ ክፍል ይወክላሉ ብለን እናምናለን፡፡ የውይይቱ ተሳታፊዎች ስለድህነት ያላቸውን አመለካከትና ከህይወት ልምዳቸው አንፃር ያላቸውን አስተሳሰቦች ከእኛ ጋር ይካፈላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከድህነት ለመላቀቅ ያደረጓቸው ጥረቶችና ያገኟቸውን ተሞክሮዎችንም ያስረዱናል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በፖሊሲ ደረጃ ምን ቢደረግ ነው ድህነትን መቀነስ የሚቻለው? በሚል ዙሪያ ያላቸውን ሀሳቦችና አስተያየቶች እንሰማለን፡፡

በሀገርና በሕዝብ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያወያይ መድረክ መክፈት የዲሞክራሲ ባህል በሀገራችን እንዲዳብር ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በመንግስት ፖሊሲ አወጣጥና በተግባር ለማዋል በሚደረገው ጥረት ተሳትፎው እንዲዳብር የሚያግዝ ተግባር ነው፡፡

ምህረት አየነው
አዘጋጅ

## Summary of Presentations

The fourth Workshop of the Poverty Dialogue Forum, which was entitled *Listening to the Poor*, and was held on 12 July 2001, marked a significant departure for FSS. For the first time in the program, FSS provided a forum to the poor to tell their own story and to participants of the program to learn about poverty from the poor themselves. The program brought together six poor people (four women and two men) from different parts of Addis Ababa to talk about their experience and how they have been able to cope with poverty. Following is a summary of the presentations.

### Poverty: What it Means

The **first speaker** was Gizachew Haile, a young man of 24 who was born and brought up in the poorest section of Addis Ketema. His family, which initially consisted of his parents, his two brothers and a sister, was very poor and his parents found it hard to support their children. As a small boy his parents sent him to the neighborhood "Priest School" not because they were keen about religious education but because it was cheap and a good means of keeping him from getting into trouble. He then attended regular school working part time to support himself. Both his parents died while he was in grade school and in his early teens, and he was forced to assume responsibility for the household. This meant doing odd jobs part time and going to school part time. After a while, his two brothers left the city to seek opportunities elsewhere which greatly reduced his family burdens. His sister, whom he was helping to go to school, dropped out and became a maid to support herself. Gizachew found it very hard to work and continue with his education and he had to drop out of school several times because of the difficult circumstances. It was only when he joined one of the credit programs run by PROPRIDE, a local NGO working in Addis Ketema and elsewhere in the city, that he was able to return to school and complete his high school education.

Gizachew characterized poverty as a malignant disease. To be poor, he said, was to lose hope, to give up on life itself. Poverty gives rise to conflict in the community and leads to crime. Poor people, he noted, suffer social exclusion. He believed that if Government and NGOs could find ways to create employment opportunities, it would be an effective way of reducing poverty. Providing skills training to the poor, he thought, would improve their chances of secure employment.

The **second speaker**, Senait Zenawi, was a young woman of 24 who was born and still lives in the Tecklehaimanot area of Addis Ababa, one of the poorest areas in the city. The family consists of nine persons: her parents, three brothers, two sisters, her son and herself. She is unmarried. Her mother is a washerwoman and her father is retired and has a small pension. Because her parents were unable to make ends meet and found it hard to care for their children, she was forced to drop out of school and seek employment at a very young age, when she was about 16. Like her mother she became a washerwoman, and for six years she earned an average of 60 Birr a month washing clothes. Moreover, as her parents were getting old and her brothers and sisters were much younger than her, she assumed responsibility for the whole family. With her meager earnings and the occasional support of her mother who continued to wash clothes to earn some income even though she was getting old, she has managed to keep her three brothers and one sister in school. Her son is too young to go to school and one other sister does not go to school because she cannot afford to pay for her. Senait said that life became increasingly hard because the income she and her mother earned (her father's pension was inconsequential) could barely cover the growing needs of the family. A lucky break for her was the chance to enroll in a training program run by Hope Enterprises, a local NGO working with the poor in the city. She is now training as a cook and housekeeper. She has also been able to benefit by the organization's micro-credit program.

Senait described poverty as the loss of respect and trust. The poor, she said, are considered the lowest of the low: they are looked down upon, not trusted, and not respected. They play a marginal role in the life of their community. Senait thought that the best way to reduce poverty was to create employment opportunities targeted to the poor. Both the Government and NGOs should make employment creation, in particular employment for the poor, as their priority if they hope to reduce poverty in the city. She was emphatic that if just

one person from a poor family has a secure job, earning a decent income, it will help bring considerable improvements in the condition of the family. Another important factor for poverty reduction, she thought, was providing education to the poor. She felt NGOs and the Government should put more resources in extending educational opportunities to the poor.

The **third speaker** was Sisay Gessesse, a young man of 25 who is now actively involved in programs run by the Forum for Street Children, one of the few local NGOs working with street children and children in difficult circumstances in Addis Ababa and a few other towns. The story of his life is similar in many ways to that of the panelists who spoke before him. Sisay was born in the Kirkos area of Addis Ababa, a neighborhood with a large population of poor households. His family consisted of nine children and his parents, but his father died when he (Sisay) was very young. As the eldest child in the family, he dropped out of school and tried to support his family by vending cigarettes, candy and gum. He soon became a street child, living off the street but not on it. Gradually, this lead to drug taking, violence and a very insecure life. For a while, he was taking hashish, snorting benzene, and chewing *qat*. Because he was young (he was barely in his teens), he was frequently victimized by the older street children, sometimes beaten and attacked. Sisay's break came when he met development agents working for Save the Children (USA) and became involved in one of their urban programs. He was about 13 at the time. Later, he joined the activities run by Forum for Street Children with whom he is still attached. Sisay noted that now he is free from drugs.

Sisay pointed out that poverty leads to the breakup of families, to social conflict, and marginalization. To be poor is to lose the trust of one's neighbors, to lose the chance to be a member of the *idir* in the neighborhood, and to be dehumanized. Sisay thought that NGOs' savings and credit programs have played an important role in improving the life of poor people. He also believed that providing skills training for the poor, especially for street children and unemployed mothers, would offer opportunities for both wage employment as well as self-employment. It was his opinion that credit services and employment for the poor would be the best method of tackling growing urban poverty.

The **fourth speaker** was Marta Tadesse whose life experience was slightly different from the rest of the speakers. Marta, who said she was 22 years old, has three brothers and four sisters, but initially her family was not quite poor but became so because of what she called an unexpected misfortune. Now, her mother does embroidery to earn an income, her father is engaged in petty business activities and she and her second sister have become petty traders. While her brothers were able to continue with their schooling, she and her sisters had to work part time in order to finance their education; one of her sisters had to drop out because she was unable to cope with school and work. To improve her earnings she managed to take training in embroidery but this has not lead to better income for herself. She has recently joined the mircro-credit program run by ProPride, a local NGO, and has benefited by it.

Marta thought poverty was the inability to work and earn a living because of the lack of access to economic assets, in particular money. Because of the lack of money, many who are capable of earning a living are not able to do so. To be poor, she said, was to lose one's humanity. Marta believed the way out of poverty was to provide credit services to the poor, to encourage trade and to provide skill training to the needy so that they can improve their employment opportunities and earning ability.

This concluded the presentation of the panelists. Dr. Konjit, the Chairwoman, then invited **Wzo Alganesh Abebe** and **Wzo. Yeshi Mohammed**, two poor women who had consented to participate in the debate and who were sitting with the audience, to make brief presentations. Wzo. Alganesh, who spoke first, said she was forty-five years old, a mother of five children and comes from a military family background. She said she has experienced the bitter fruit of poverty and had once reached a stage where she could not support her children nor send them to school. She is a lone parent but she was fortunate in that a few years back the Forum on Street Children helped her eldest daughter to pursue her education. This, she said, lifted a great burden from her. Her daughter is now in secondary school. Moreover, through the support of the Forum she became involved in a credit program together with other women in her neighborhood. She said she was the first member of her credit group to take out a loan. The program has been of considerable benefit to her. She has so far taken three loans and has used all of them to good effect. She thought that one way to reduce poverty was to provide poor people interest-free loans to enable them

to invest it and be economically active. Interest on loans, she thought, was a burden on the poor and tends to discourage them from using their loans effectively.

Wzo. Yeshi, the other speaker, said she was born and grew up in Wollo. She did not say how old she was but our estimate is that she is in her early thirties. She migrated to Addis Ababa and initially found work in one family's home. She had her first child while working with this family as a maid. Then she moved to one of her relative's home, became a fuelwood carrier and had her second child. It was hard, she said, bringing up two children with income from the sale of fuelwood. From time to time she baked *injera* to earn more income. The relative with whom she was staying wanted her to take her two children and go back to Wollo but she refused and had to move out of the house. After persistent petitions to officials of her Kebelle, she finally succeeded in getting a small "house". However, she said, the house was a flimsy structure and had virtually no roof. One day when it rained hard the house collapsed and almost killed on of her children. Her only source of income was still fuelwood vending and bringing up two children on such small income was very difficult for her. She wanted both her children to go to school but she did not have the means to pay for the education of both of them. Then, about three years ago, she met development agents from ACCORD, an NGO working with the poor in urban areas, who encouraged her to join a savings and credit group organized in her neighborhood. She joined the group and has been able to take out loans several times. She said she has benefit a great deal because from the program. She has been able to send both her children to school and her eldest son is now in 11th grade. She now bakes and sells bread and this has improved her income. She believed the kind of micro-credit program she has been involved in is of great benefit to poor people.

**Poor People's Views of Poverty and Poverty Reduction**

What came out of the discussion was that the poor have clear views of what it means to be poor what must be done to reduce the level of poverty in the urban areas. To the poor, poverty was not primarily an economic phenomenon. Only one speaker, Marta Tadesse, defined poverty in terms of lack of access to economic assets. Poverty for the rest was a social and human problem. To be poor was to be dehumanized, to lose the respect and trust of one's neighbors, to be marginalized and socially excluded. Asked about the causes of poverty, many of the panelists cited the following as major contributing factors:

a) lack of employment opportunities, and of employable skills;

b) large family size and the inability to practice family planning;

c) lack of access to education.

All the speakers had something to say about what must be done to bring about improvements in the life of the poor and to reduce the level of poverty in the urban areas. They were all aware that there are far too many poor people in the country. None of them believed that poverty was ordained by God. They were of the opinion that it was possible to improve one's status through one's effort, given the opportunity. They were conscious that sound programs by Government and NGOs can go a long way to help reduce poverty. The programs that were frequently cited as being critical to the effort to reduce urban poverty were the following:

a) **Employment schemes for the poor**. For this, both NGOs and Government agencies need to promote skills training, specially targeted to young people, women, and the unemployed. By employment opportunities the speakers were referring not so much to civil service jobs but rather to skills-based employment in manufacturing, construction, or the occupational trades.
b) **Access to education for the poor**. All the speakers regarded education as a way out of poverty. But education was costly and most poor families are unable to pay for their children's schooling. Programs that help the poor to keep their children in school were therefore considered to be very important.
c) **Access to credit services for the poor**. Many of the speakers had benefited by the credit program of the NGOs with which they were involved. Sound savings and credit programs therefore were seen as an important lifeline for the poor.

What follows is the full text of the presentations in Amharic.

# የውይይቱ አቅራቢዎች ከመድረክ

## *<u>አንደኛ አቅራቢ፣ ግዛቸው ኃይሌ</u>*

እኔ ስሜ ግዛቸው ኃይሌ ታህሳስ 1969 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ አዲስ ከተማ ተብሎ በሚጠራው ወይም ወረዳ 5 ቀበሌ 15 እጅግ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ህፃናትና ደሀው ኅብረተሰብ በሚገኙበት በአንዲት አነስተኛ መንደር ከአባቴ ከአቶ ኃይሌ እና ከእናቴ ከወ/ሮ ጥሩነሽ ከሚባሉ ሁለት ግለሰቦች በአንዲት ደሳሳ ጎጆ ቤት ውስጥ ተወለድኩ። እድሜዬ ለትምህርት እንደደረሰ በአቅራቢያዬ ከሚገኙ መምሬ ገ/መድኅን ተብለው የሚጠሩ አንድ አባት የአካባቢዬ ሰዎች በጣም የሚወዷቸው የቤቱ ዙሪያ በካርቶን፣ ሳጠራ እንዲሁም በላስቲክ በተወጠረ በውስጡ ብዛት ያላቸው ህፃናት ተማሪዎችን በያዘች ትንሽ ክፍል ቤት ውስጥ ገብቼ የቄስ ትምህርቴን መማር ጀመርኩ። የቄስ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በእዛ አካባቢ በወረዳ 4 ቀበሌ 26 ክልል ውስጥ በሚገኝ አሜድላ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በመግባት መማር ቀጠልኩ። ይሁን እንጂ ወላጆቼ የትምህርት ጣዕምን አውቄ ሳይሆን እንዲሁ በመላ የአካባቢው ህፃናት ደብተራቸውን ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ በማየት ይመስለኛል እኔንም የላኩኝ። የማስተማሩን ሂደት ግን ሊቀጥሉበት አልቻሉም። እናም ከአራተኛ ክፍል ለማቆም ተገደድኩ። ትምህርቱን ለማቆም የተገደድኩበት አብይ ምክንያት ከእኔ በላይ ሁለት ወንዶች ልጆች ስለነበሯቸው በተጨማሪ ከእኔ በታች አንዲት ሴት ልጅ ስለነበራቸው ነው። በጠቅላላው አራት ልጆች ከወላጆቼ ጋር ስድስት ነበርን። ቤተሰቦቻችን ሁላችንንም ለማስተማር አቅሙ አልነበራቸውም። ምንም እንኳ እናታችን ቅጠል ሽጣ እንጀራ ጋግራ የምታገኘው አነስተኛ ገቢ በመሆኑ አባታችንም ቤተሰቡን የሚደጉም ስራ የሌለው ስለነበር የእኛነታችን የኑሮ ደረጃ በምንም መልኩ ሊሻሻልና ሊለወጥ አልቻለም።

ይህ ችግር ለአራት ዓመታት ያህል ባለመቋረጡ ከዚህ በኃላ ወላጆቼ በኑሮ አለመመቻቸት ምክንያት የህሊና እረፍት ማጣት፣ ራስን መግዛት አለመቻል፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ልጆችን በዕቅድ አለመውለድ፣ እንዲሁም በሚያገኟ ት ጥቂት ገንዘብ በዕቅድ አለመመራት ሌሎችም ምክንያቶች ተደራርበው በጣም ደካማ ለሆነ በሽታ ተዳርገው ራሳቸውን ማቋቋም ተስቸው ሁለቱም ተራ በተራ ይህችን ዓለም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበቷት። በእንዲህ ሁኔታ እያለን ታላላቅ ወንዶች ልጆች በጣም አስጊው ክስተት በጣም ስላስቸገራቸው በጣም ደነገጡ። ግን በፀጋ መቀበል ነበረባቸው። የራሳቸውን አቅጣጫ ቀየሩና አንደኛው በወቅቱ ደርግም ነበር በውትድርና ዓለም ውስጥ ገባ። ሌላኛው ደግሞ ከከተማ በመውጣት የራሱን ኑሮ መኖር ተገደደ። ከዚህ በኃላ ነበር እኔና እህቴ ያለብንን የቤተሰብ ኃላፊነት የተረከብነው። ታናሽ እህቴን ይገዜ ትውልድ ስፍራችንን በመያዝ ከኑሮ ጋር ግብግብ፣ ትንቅንቅ፣ ትግል ተያያዝን። እኔና እህቴ በአንድ ጎጆ ውስጥ በመሆን ቤተሰቦቻችን ያስረከቡንን ያንን የትግል ኑሮ እየኖርን እኔም የጉልበት ስራ እየሰራሁ እሷ በቤት ጠባቂነት ለአራት ዓመት በዚህ ሁኔታ ኖርን። ይሁን እንጂ እሷ መማር ስለነበረባት እኔ የጉልበት ስራ እየሰራሁ እሷን መስተማር ቀጠልኩ። ቢሆንም ይህም ለሁለት ዓመታት ነበር የዘለቀው። ከዚህ በኃላ ግን አቅሜ ስላልቻለ ትምህርቷን እንድታቆም ተገደደች። ከዚህ በኃላ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ነበረብኝ። ይኸውም ከሷ ጋር በመስማማት እኔ በጉልበት ስራ በመተዳደር እሷ ግን በሰው ቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ ራሷን እንድትችል ወሰንኩ። ሳትወድ በግድ አቅሟ ሳይፈቅድላት ያለፈቃደኝነት ያለአቅሟ ከቤት ተሰናብታ ወጣች። ከዚህ በኃላ እኔ በጉልበት ስራ እየተዳደርኩ ትምህርቴን ቀጠልኩ። ትምህርቴን በዚህ ሁኔታ ለአራት ዓመታት ያህል ተምሬ ስምንተኛ ክፍል ለመድረስ በቃሁ። ነገር ግን የብቸኝነትን ኑሮ ልገፋው አልቻልኩም። እህቴ ከእኔ ጋር መሆን እንዳለባት ወሰንኩና አስመጣኋት። ከእኔም ጋር አብራ መኖር ጀመረች። እሷም ትንሽ ስራ እየሰራች እኔም የጉልበት ስራ እየሰራሁ ትምህርቴን በመማር ላይ እያለሁ በአጋጣሚ አንድ ችግር ተከሰተ። ይህ ችግር ሁለታችንንም አስደነገጠን። ነገር ግን እዚህ መድረክ ላይ ልገልፀው አልፈልግም። ይህን ለራሴ እተወዋለሁ። ከዚህ በኋላ በዘጠነኛ ክፍል ትምህርቴን ለመጀመር ወሰንኩ። ኑሮ በጣም ስለከበደኝ የስራዬን መስክ ለመቀየር በጣም ተቸገርኩ። ነገር ግን በወቅቱ ይኼ ፕሮፕራይድ የሚሉት ምግባረ ሰናይ ድርጅት ነበር። ይሄ ድርጅት መቋቋሙ ነበርና የዚህ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ዓላማውን ለማወቅ ፈለኩ። ጠይቄም በመረዳት ያለብኝን ሁኔታ በመግለፅ ለአነስተኛ ፈጠራ የሚውል ብድር ለማግኘት ቻልኩ። ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ስራዬም እየተሻሻለ ቀስ በቀስ ሰው መሆን ጀመርኩ። ከዚህ በኋላ አቋሜው የነበረውን ትምህርቴን ለመቀጠል ፈለኩ። የመማሪያ መሳሪያዎች ከሞላ ጎደል ገዝቼ ዳግም እዚሁ አዲስ አበባ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተብሎ በሚጠራው ከዘጠነኛ ጀምሮ ያለው ት/ቤት ለመማር ፈለኩ። ከዚህ በኋላ ትምህርቴን ጨረስኩ። እህቴንም በአነስተኛ የስራ መስክ እንድትሰማራ ራሷንም እንድትችል በማድረግ ዛሬ ጋሻ ተብሎ በሚጠራው በአነስተኛ ብድር አቅራቢ አክሲዮን ማኅበር ድርጅት ጋር በመተባበር ኑሮዬን

በሚገባ ትምህርቴንም በመቀጠል ለመምራት ወሰንኩ::

እነሆ ዛሬ እግዚአብሄር ይመስገን እዚህ ደረጃ ደርሻለሁ:: እግዚአብሄርም ወዶና ፈቅዶ ትምህርቴንም ጨረስኩ:: እራሴንም በሚገባ መምራት ችዬ ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር ማኅበራዊ ኑሮ መስርቼ አሁንም እራሴን ጨምሮ ሁለት ታናናሽ እህቶቼን ይዤ በመልካም ኑሮ ላይ እገኛለሁ:: እግዚአብሄር ይመስገን ታሪኬንም በአጭሩ እዚህ ላይ አበቃለሁ::

ግን ባሳለፍኩት ባየሁት እንደተረዳሁት ከሆነ ግን ትንሽ ለማለት የምሞክረው አንድ ሃሳብ አለኝ:: በመሰረቱ ይህ ድህነት የሚሉት ነገር እኔ እንደማስበው የስጋ ደዌ በሽታ ነው:: ለምን በህይወቴ ስለመጣ ብቻ ነው:: ምክንያቱም በበሽታው የተያዘ ሰው ብንመለከት የማዘን የመተከዝ ተስፋ የመቁረጥ ራሱንም ከምንም በታች በማድረግ እንዲሁም ዓለም ፊቷን ያዞረችበት ይመስለዋል:: በልቡ መልካም አይመኝም:: ጥሩ ነገር ሰርቶ ለማለፍ አይፈልግም:: ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በማኅበራዊ ኑሮ አይተባበርም:: ከቤተሰብ ጋርም አይስማማም:: ከትውልድ ቀዬው የግድ መሸሽም መሰወርም ይመርጣል:: በዚህ መልኩ ድህነት ከዚህ የሚተናነስ አይደለም:: እንዲያውም ድህነት ኃጢያትን ያሰራል፣ የሰውን ያስመኛል፣ ሰውን በክፉ ለመጣል ያነሳሳል፣ ወንጀልንም ያሰራል:: ታዲያ ወገኤ ድህነት የሚሉት መከራ ስቃይ ጉስቁልና የበዛበት ህይወት ነው ድህነት ካለ ከነዚህ ሁሉ ግብረአበሮቹ አብረውት ይኖራሉና ሰው ይህንን ህይወት እንዳይገጥመው ተስፋ ባለመቁረጥ በመትጋት የሚመጣውን መከራ ችግር በፀጋ መቀበል እራሱ ከማንም እንደማያንስ ማመን አለበት:: ለሰዎች ታማኝ ቅን አገልጋይ መሆን አለበት:: ሰዎች የደረሱበት ሁሉ እደርሳለሁ ብሎ ማመን ከሰራ ማግኘት እንደሚችል ካገኘም ኑሮው እንደሚሻሻል ማወቅ አለበት:: ኑሮው ከተሻሻለ ደግሞ ጥሩ ዜጋ ማፍራት እንደሚቻል ማመን አለበት:: ሌላው ደግሞ ዛሬ በአገራችን ብዙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ:: ከነዚህ ድርጅቶች ለመጥቀስ ያህል እንደ ጋሻ፣ ተስፋ ድርጅት፣ አኮርድ ኢትዮጵያና የመሳሰሉ ሌሎችም ድርጅቶች አሉ:: ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር የራስን ድህነት አይደለም በሀገራችን ላይ ተንሰራፍቶ የሚታየውን ድህነት እንዳለ ለማጥፋት ባይቻል እንኳ መቅረፍና መከላከል የሚቻልበት ዘዴ አለ:: ሌላውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ የስራ መስኮች ቢያስፋፉ ለምሳሌ ዕደ ጥበብ በአነስተኛ ክፍያ የሙያ ት/ቤቶችን በማሰራት ኅብረተሰቡን ስራ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ ቢፈጠር ድህነት ሊቀረፍ የማይችልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም:: ለምሳሌ ያህል ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነገር ቢኖር ጋሻ አነስተኛ የብድር አክሲዮን ማኅበር ብንመለከተው ደሀው ኅብረተሰብ በአነስተኛ ወለድና በረጅም ጊዜ ክፍያ የሚያልቅ ብድር በመስጠት ህፃናትን ሰብስቦ በማስተማር የጤና ትምህርት በመስጠት የተለያዩ የልማት ስራዎችን በመስራት ቁጥራቸው እጅግ በዛ ያሉ ሰራተኞችን በማቀፍ የአካባቢውን ደሀ ኅብረተሰብ ጥሩ አገልግሏል ብዬ አምናለሁ:: ሌላው ደግሞ ምንድነው ይሄ በዚህ ሳያበቃ በጎን የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ይህንንም ልመሰክርለት እወዳለሁ:: ሌላው ደግሞ ድህነት ሊቀረፍ ይችላል ብዬ የማምነው ኑሮን በፕሮግራም ልጆችን በዕቅድ ወልዶ ማስተማር የሚቻልበትን ዘዴ ከኅብረተሰቡና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለወደፊቱ ኑሮ ጥሩ ይሆናል ብዬ አምናለሁ:: ግን ልናገረው የምፈልገው አንድ ነገር አለ:: ይኸውም ባሳለፍኩት ጊዜ ህይወቴን፣ የኑሮዬን ሁኔታ እንዲህ አድርጌ በግጥም አስቀምጫለሁ:: የግጥሙም ርዕስ 'ዓለም' ብየዋለሁ::

ዓለም ዓለም እጅግ ደስ ትላለች፣
ጠለቅ ብለው ሲያዩት በጣም አንገሽጋሽ ናት::
አፍአዊ አቋም በጣም አሸብራቂ፣
ውስጣዊው ይዘቷ እጅግ አሰቃቂ::
በአሸብራቂ መልኳ ሰውን ትስባለች፣
እስካለሁ ልጆቼ አይዟችሁ ትላለች፣
በመጨረሻ ላይ ጥላ ትጠፋለች::
በዚህ ዓለም ላይ ሆነን ስንመለከተው፣
የዓለምን ከንቱነት መረዳት ቅርብ ነው፣
የአብለጭላጭ ጌጦች ውበትን ስናየው፣
አበባው አብቦ እንደሚረግፍ ነው::
ስለዚህ ወገኖች በደንብ እናስተውል፣
የህይወትን መንገድ መያዝ ይበጀናል::
ጋሻን አስከትለን በዕቅድ ስንኖር ነው፣
ዓላማውን ጠይቀን ካወቅን ሚስጥሩ፣
ድህነትን ማጥፋት ነው ከነግብረአበሩ::
ጋሻን ተመልክተን በደንብ ከሰራን፣
ከቶ አይሳነንም ድህነትን ማጥፋትን::
በእርሻ በእጅ ስራ ኑሯቸውን መርተው፣
የተጠቀሙትን እስቲ እናስታውሳቸው፣
ሳይሰሩ አይደለም ዕድሜያቸው ያለፈው::

አመሰግናለሁ::

*ሁለተኛ አቅራቢ፣ ሰናይት ዜናዊ*

*በመጀመሪያ እድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ:: ስሜ ሰናይት ዜናዊ ይባላል:: የተወለድኩት በ1969 ዓ.ም. እድሜዬም 24 ነው:: ተወልጄ ያደኩት እዚሁ አዲስ አበባ በተክለሃይማኖት አካባቢ በወረዳ 3 ቀበሌ 44 ልዩ ስሙ ስልጤ ሰፈር በሚባለው ነው:: እናትና አባቴ በህይወት አሉ:: የትምህርት ደረጃዬ 11ኛ ክፍል ነው:: እድሜዬ ለትምህርት እንደደረሰ ቄስ ትምህርት ቤት ተምሬ ከ1ኛ-8ኛ እድገት በሥራ ተማርኩ:: ከ9ኛ-11ኛ በሽመልስ ሀብቴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማርኩ::*

*ሦስት ወንድሞችና ሁለት እህቶች አንድ ልጅ ሲኖረኝ አንድ ወንድሜ ግን በድንገት በመኪና አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶናል:: አሁን በአጠቃላይ አራት ወንዶች ከእናት ከአባቴ ጭምር በአጠቃላይ ስምንት ነን:: ሁለት ወንድሞቼ ይማራሉ:: ማለት ሁሉም ይማሩ ነበር ከልጄ በስተቀር:: እህቴ ግን በቤታችን ውስጥ ባለው የኑሮ አስከፊነት ትምህርቷን ልታቋርጥ ተገዳለች ትንሿ እህቴ ከሶስተኛ ክፍል አቋርጣለች:: ልጄም አይማርም:: አባቴ በፊት ስራ ነበረው:: ጡረታ ከወጣ ወደ ስምንት ዓመት ሆኖታል:: የጡረታውም ብር 78 ሲሆን ቤቱን የማስተዳድረው እኔ ነኝ:: አባቴ ጡረታ ሲወጣ እናቴ በየሰዉ ቤት ልብስ አጥባ እንጀራ ጋግራ ነበር የምታኖረን:: በአጋጣሚ እናቴም አባቴም ይታመሙና ቤቱን ማስተዳደር እኔ ጀመርኩ:: እስካሁን እስካለሁበት ሰዓት እኔ ነኝ የማስተዳድራቸው:: እናት እና አባቴ ግን እግዚአብሔር ይመስገን ተሽሏቸዋል:: በአባቴ ጡረታ መውጣትና በቤታችን ችግር ትምህርቴን ከ11ኛ ክፍል ለማቆም ተገደድኩ:: ትምህርቴን ትቼ የቤቴን ኑሮ መግፋት ስለነበረብኝ በ1986 ዓ.ም. ትምህርቴን አቋርጬ በየሰዉ ቤት ልብስ አጠባ እንጀራ ጋገራ ስራ ባለመምረጥ ያገኘሁትን እየሰራሁ ኑሮዬን መግፋት ጀመርኩ:: እቤት ማስተዳደር ከጀመርኩ አሁን ስድስት ዓመት ሆኖኛል:: ስድስት ዓመት ሙሉ በየሰዉ ቤት የሰውን ፊት እያየሁ ያገኘሁትን ስራ ባለመናቅ እግዚአብሄር እስካቆየኝ ኖሬአለሁ:: ትምህርቴን ግን መቀጠል አልቻልኩም:: እኔ የደረስኩበት ውንድሞቼን ማድረስ ግድ ስለሆነ በማገኘት ገቢ ወንድሞቼን ማስተማር ቀጠልኩ:: እንደዛም ሆኖ ወንድሞቼን ሁሉ ማስተማር አልቻልኩም:: ሁለት ወንድሞቼንና አንድ እህቴን እያስተማርኩ ነው:: አንድ እህቴ ግን የግድ የምከፍልላት ስለሌለ የቤት ኪራይ፣ መብራት፣ ውሃ በእኔ ስለተጫነ ቤተሰቦቼም እኔን ስለሚጠብቁ የቤት ኪራይ፣ የመብራት ኪራይ፣ ካልከፈልኩ ደግሞ መኖር ስለማልችል እስካሁን እስካለሁበት ሰዓት ኑሮዬን ለማሻሻል እጥራለሁ:: ኑሯችን ግን ምንም ሊሻሻል ለውጥም ሊያመጣ አልቻለም::*

*እኛ እያደግን በሄድን ቁጥር የሆዳችን መጠን እየጨመረ ነው የሄደው:: ልጄም እያደገ ሲሄድ ልብስና ጫማ ስለሚያስፈልገው ሰውም ልብስ ሳይለብስ ራቁቱን እንደማይሄድ ሁሉ እሱን መሸፈን ስላለብኝ እንደዚህ እያልኩ በየሰው ቤት በወር ከማገኛት 60.00 ብር እናቴም ትንሽ ከምታገኛት ከአባቴ ጡረታ ጋር ቤት ውስጥ ያለውን ነገር እንዲህ እንሸፍነዋለን:: እነዲህም እያልን እስካሁን ኖረናል:: በአጋጣሚ ቤተክርስቲያን ልሳለም ስሄድ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት (ኮንሰርን) ሲመዘግቡ አየሁና መዝግቡኝ አልኩ ባላሰብኩት አጋጣሚ ማለት ነው ዘንድሮ 1993 ዓ.ም. ጠርቶ በተስፋ ድርጅት ት/ቤት በቤትና በምግብ አያያዝ እያስተማረኝ ነው:: ሲያስተምረኝም ለትራንስፖርትና ለምሳ ሳንቲም እየሰጠኝ ነው:: ተምሬም ስጨርስ ምን እንደምሆን አላውቅም:: በሙያዬ ወይ ስራ ያስይዘኛል ወይ አያሲዘኝም:: ግን በማየው ነገር ከእኔ በፊት በተማሩት ልጆች ጥሩ ፍሬ ላይ ሲያደርሳቸው ስለማይ እኔንም እንደዛው እንደሚያደርሰኝ ተስፋ አለኝ::*

*በአጠቃላይ ድህነት ማለት በጣም አስከፊ፣ አስቸጋሪ፣ ከሰው እኩል የማያስኬድ፣ በምኖርበት ሰፈር የሚያውቀኝም የማያውቀኝም አዋርዶኝ፣ ትንሽ ሰው አድርጎኝ ኖሪያለሁ ድሃ ሲባል ሌባ አጭበርባሪ በአጠቃላይ በመጥፎ የሚታይ ነው:: ከጎረቤቶቼ አቅም እማያቸው ጥሩ አይደሉም:: ድሃ ሲባል የሚሰርቃቸው፣ ቆሻሻ፣ ሲያዩት ሰርቆ ከቤታቸው የሚወጣ ማለት ነው:: ከማየው ከአካባቢዬ ድህነትን መግለፅ በጣም ያስቸግረኛል:: አሁን ግን ኮንሰርንን ይህን እድል ሰጥቶኝ እንድማር ስላደረገኝ ማመስገን እፈልጋለሁ:: በዚች በምማራት ከእግዚአብሄር ጋር ስራ ያስይዘኛል ብዬ አምናለሁ:: በመጨረሻ ግን ይህን እድል አግኝቼ እንድናገር ስለተፈቀደልኝ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የምለው ነገር ይኖረኛል:: በሚያገኘው አጋጣሚ የስራ ዕድል ሲኖር ከአንድ የድሃ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው ስራ ቢይዝ የቤተሰቡን ኑሮ ማሸነፍና የዕለት ጎሮሮውን መሸፈን ስለሚቻል በተቻለ መጠን ከላይ የጠቀስኳቸው ድርጅቶች የድሆች ቤተሰቦችን ፈልገው ቢያስገቡ እናም አሁን በያዙት ዓላማ ቀጥለው የድሆችን ቤተሰቦች መማር እየፈለጉ ስለሆነ በተቻለ መጠን እንዲያስተምሯቸውና እንዲረዷቸው መልዕክቴን አስተላልፋለሁ::*

## *ሶስተኛ አቅራቢ፣ ሲሳይ ገሠሠ*

እኔ ይህንን ዕድል በማግኘቴ ደስ ይለኛል። ምክንያቱም ብዙ ነገሮች አሳልፌያለሁ፣ ብዙ ችግሮች ደርሰውብኝ ዛሬ ለዚህ በቅቻለሁ። በጎዳና ላይ ስኖር ያሳለፍኳቸውን ችግሮች ዛሬ እዚህ ደረጃ ላይ እንዴት እንደደረስኩ ለመግለፅ ዕድሉ ስላጋጠመኝ በድጋሚ አመሰግናለሁ።

እኔ ወጣት ሲሳይ ገሠሠ የተባልኩ በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ በተለይም ቂርቆስ አውራጃ በሚባለው ተወልጄ ያደኩ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በሽመልስ ሀብቴ በአንደኛ ደረጃ እንዲሁም በወንድማማቾች የህዝብ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምሬያለሁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በመማር ላይ እገኛለሁ።

ለቤቴ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ። ከእኔ በታች ስምንት ልጆች አሉ። እንግዲህ አስተዳደጋችንም ትንሽ ቤተሰቦቼ ብዙ በትምህርት የገፉ ስላልሆኑ የስምንት ወር ወይም የአንድ ዓመት ርቀት ቢኖረን ነው አወላለዳችን። በአሁኑ ሰዓት ዕድሜዬ 25 ዓመት ሞልቶኛል። የማስተዳድረው የቤተሰብ መጠን ከእኔ ጭምር ዘጠኝ ነን። እንግዲህ እነዚህን ቤተሰቦችን ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ እየረዳሁ ነው። ከዚህ በፊት አባታችን ከመሞቱ በፊት ደሃ ባንባልም በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ የምንገኝ ነበር። አባታችን በግለሰብ ጋራዥ ውስጥ ይሰራ ነበር። በህመም ምክንያት የጋራዡ ኃላፊ ኪሳራ ደርሶብኛል ብሎ ጋራዡን ዘግቶ ሲሄድ አባታችንም በብስጭት ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል። እኛም ችግር ውስጥ ገባን። እናቴም ደካማ ነች። የሁለት ወር ኦፐራሲዮን እንደሆነች አባታችን ይሞታል። ከቤት የመጀመሪያው ልጅ ስለሆንኩ ትምህርቴን አቁሜ በስታዲየምና በለገሀር አካባቢ ሲጋራና ማስቲካ እየሸጥኩ ለቤተሰቦቼ በቀን ከ5-10 ብር በመስጠት አስተዳድር ነበር። በኃላ ማስቲካና ሲጋራ በመሸጥ ላይ እያለሁ ብዙ ችግሮች ነበሩብኝ። ንብረት ይቀማል፣ መደብደብ አለ፣ ከአቅም በላይ በጎዳና ተዳዳሪዎች ገንዘብ መቀማት አለ፣ እንግዲህ እነዚህን ነገሮች መጋፈጥ ስላልቻልኩ እነሱን ተመሳስዬ ቤተሰቦቼን መርዳት ትቼ ኑሮዬን ጎዳና ላይ አደረኩ። በወቅቱ ብዛት ያላቸው የዕርዳታ ድርጅቶች በ1979 ዓ.ም. በምንኖርበት ጎዳና ላይ እየመጡ የምክር አገልግሎት እየሰጡን ራሳችን ሰርተን እንድንችል የገንዘብ እርዳታ ያደርጉልን ነበር። በጎዳና ላይ እያለሁ ብዙ ችግሮች ደርሰውብኛል። የጤና መታወክ ችግር፣ የምግብ ፍላጎት አለመሟላት፣ በሰዎች የመጠላት፣ ትምህርት አለማግኘት፣ እንደ ልዩ ፍጡር መታየት፣ በዛ ላይ ሰዎችን በምንቀርብበት ሰዓት አለመታመን ሙሉ በሙሉ የጎዳና ተዳዳሪ ዝናም ለመጠለል ጥግ ስንይዝ ብዙ ሰዎች ይርቁን ነበር። ብዙውን ጊዜ በሱስ የመጠመድ ባህርይ ይታያል። እኔም በሱስ ተጠምጄ ነበር። እነዚህን ሁሉ ችግሮች ለማለፍና ለዚህ የበቃሁት ዛሬም እናንተ ፊት ቆሜ የምታዩኝ የተመጣጠነ ምግብ ያው በቤተሰቦቼና በሴቭ ዘ ችልድረን በሚባለው የአሜሪካ የህፃናት አድን ድርጅት በ1980 ዓ.ም. በአቶ ፋሲል ወልደማሪያም በሚመራው የእርዳታ ድርጅት ነው። በስራ አጋጣሚ ስታዲየምና ለገሀር አግኝተናቸው መብራት አካባቢ ላይ የፕሮግራሙ ተሳታፊ እንዲያደርጉን በጠየቅናቸው መሰረት ፈቃደኝነታቸውን ገለፁልን። ከዚያም በኃላ የዛው ድርጅት ተጠቃሚ ሆንን። በድርጅቱ ውስጥ የምክር አገልግሎት ይሰጡን ነበር፤ ሁሉን ነገር ያሟሉልናል፤ እንግዲህ ከዚያን በኃላ ነው የባህሪ ለውጥ፣ በማምጣት ከተለያዩ ሱሶች የተላቀኩት፤ ከቤተሰብ ርቄ ነበር አስታርቀውኛል።

ብዙ ሱሶች ነበሩብኝ። ከቤንዚን፣ ከሀሺሽ፣ ከሲጋራ፣ እስከ መጠጥ እስከ ጫት ድረስ እኔ ምንም ያልቀመስኩት ነገር የለም። ዛሬ እነዚህን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ትቻቸዋለሁ። አሁን ችግሮች አይገጥሙኝም። ከሱሶች ነፃ ነኝ። የመጠለያ ችግር የለብኝም፣ የጤንነት ችግር የለብኝም ትልቁ የጎሊና እረፍት ያገኘሁት በሰዎች ዘንድ የመታመንን ዕድል ማግኘቴ ነው። ድሮ ጎዳና ላይ ሆኜ የሚያርቁኝ ሰዎች ዛሬ እዚህ ሲያዩኝ እንደትልቅ ነገር ነው የሚያዩኝ ትልቁ ነገር በሰዎች ዘንድ የመታመን እድል ስላገኘሁ ደስ ይለኛል። የማኅበራዊ ችግሮችን ከድሃው ኅብረተሰብ እና ከፍ ካለው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር እጋራለሁ። በአሁኑ ሰዓት የምኖረው ኑሮ ጥሩ ነው። አሬም ይኼ የሆነበት ምክንያት አሁን የጎዳና ተዳዳሪዎች የህፃናት ወዳጆች ማኅበር ውስጥ እሰራለሁ። እንግዲህ እነዚህን ሁሉ ችግሮች አልፌ ነው ዛሬ ለዚህ የበቃሁት። በአሁኑ ግዜ ቤተሰቦቼን ከመርዳት አልፌ ራሴን በራሴ በማስተዳደር ላይ እገኛለሁ።

እንግዲህ ሁልጊዜ ቤተሰብን አንድ ሰው አይረዳም። የተወሰነ ዓመት ይረዳል። ከዚያ በኃላ እኔ ማን ነኝ? የሚለውን ደግሞ መፈለግ አለበት። ስለዚህ እኔም ከ1980-1993 ድረስ በመርዳት ላይ እገኛለሁ። ከቤተሰቦቼ ተለይቼ ብወጣም አንድ ለራሴ የማደርግ ከሆነ ለቤተሰቦቼ ተቆራጭ እንደውም ከፍ አድርጌ በመስጠት ላይ እገኛለሁ። ሌላው ታናሽ ወንድሜ እኔ ትምህርቴን አቋርጬ እሱ አንድ የእርዳታ ድርጅት አግኝቶ አራት ዓመት ያህል ኮርስ ወስዶ ካጠናቀቀ በኃላ እንግዲህ አንተ ይበቃሀል ራስህን ቻል ከአሁን በኃላ ደግሞ ኃላፊነቱ የእኔ ነው ኃላፊነቱን እሸከማለሁ ብሎ በአሁኑ ሰዓት እየተጋገዝን እናታችንን እንረዳታለን። ሌሎች ታናናሽ

ወንድሞቼ የአስረኛ ክፍልን አጠናቀው አሁን ቁጭ ብለዋል፡፡ እንግዲህ ከታች አንድ የእህት ልጅና የእኛም የመጨረሻ ልጅ አለ፡፡ እቤት ውስጥ እነሱ ናቸው ተማሪዎች፡፡

እንግዲህ በአጠቃላይ ድህነት ጥሩ ጎን እንደሌለው ማንም ሰው ያውቀዋል፡፡ ስለሆነም ዛሬ ለዚህ የበቃሁት በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቄ ነበር፡፡ ድህነት ቤተሰብን የሚበታትን፣ አለመስማማትን የሚያመጣ ትልቅ ችግር ሲሆን በሌላው በኩል የቤተሰብ መበታተንን፣ አባትና እናት እንዳይስማሙ፣ እህትና ወንድም እንዳይስማሙ ያደርጋል፡፡ ድህነት ሌላው ህፃናትን ወደጎዳና ያስወጣል፡፡ ከተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች ያርቃል፡፡ አንድ ሰው እድር መግባት ሲችል ደሀ ከሆነ ምንም የትም ቦታ መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ እድር ዝም ብሎ አይገባም፡፡ የተወሰነ ሳንቲም ክፍያ አለው፡፡ ያንን ሳንቲም ግን የማይከፍል ከሆነ አይገባም እናውቀዋለን ሁላችንም ጎረቤት ጥሩ ነገር የሚያደርግ ከሆነ በድህነታችን ምንም ማድረግ ስለማንችል ከጎረቤት እንሸሻለን፡፡ ይህም በአካባቢያችን የምናየው ነባር ነገር ነው፡፡ ከሰው በታች ያደርጋል፣ ተስፋ ያስቆርጣል፣ ለብስጭት ይዳርጋል፡፡ በድህነት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ኑሯ ቸውን ስንመለከት ይሔን ይመስላል፡፡ ሁላችንም በአካባቢያችን የሚገኙ የድሃ ኅብረተሰብ ክፍሎች አሉ፡፡ እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ኑሯቸውን የሚመሩት አንደኛ በተለያየ የንግድ ስራ፣ በሴተኛ አዳሪነት ኑሯቸውን የሚገፉና ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ አሉ፡፡ ይህም የምናየው ነው፡፡ የቀን ስራ በመስራት በልመና ስራ ልጆቻቸውን በማሰማራትና እነሱም በልመና በመሰማራት ከአካባቢያቸው ርቀው ሌላ ቦታ ሄደው በመለመን፣ ዕቃ በመሸከም፣ ልጆቻቸውን ትምህርታቸውን እንዲያቆሙ በማድረግ፣ እሰው ቤት በማስቀጠር፣ ሌላው ድለላ በመስራት ወዘተ… ስራዎችን እየሰሩ ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩ አያሌ የድሀ ኅብረተሰብ ክፍሎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ እኔን ከዚህ የድህነት አዘቅት ውስጥ እንድወጣ ያደረገኝ ያው ቅድም እንደነገርኳችሁ ሴቭ ዘ ችልድረን የአሜሪካ የህፃናት ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ ሲቋቋም ብዛት ያለን ወጣቶች ከጎዳና ላይ አንስቶ ተቋም ውስጥ ከተተን፡፡ ወደ 70 የምንጠጋ ወጣቶች የቆዳና የእንጨት ስራ ዎርክሾፕ ተከራይቶ መምህራን ቀጥሮልን ይህንን የሙያ ትምህርት አስተማሩን፡፡ ብዙ ወጣቶች በአሁኑ ሰዓት ራሳቸውን እያስተዳደሩ ነው፡፡

በቆዳ ስራ የምታዩዋቸው በብዛት ባዛር ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚያ የባዛር ስራዎች የእነዚህ ወጣቶች የስራ ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ከኔ ጋር አብረው ተምረው ሰልጥነው እራሳቸውን እያስተዳደሩ አልፎ ቤተሰቦቻቸውን እያስተዳደሩ ነው፡፡ እነዚህ ልጆች ከዚህ በፊት ምን ነበሩ እንደኔው ጎዳና ተዳዳሪዎች ነበሩ እስታዲዮም እና ለገሃር አካባቢ ከብሔራዊ አንስቶ ባለው ጎዳና ላይ ነበሩ፡፡ ለዚህ ደረጃ የበቃን ግማሾቻችን ደግሞ ይህ ድርጅት በሹፍርና ሰልጥነን መንጃ ፈቃድ አውጥተን በማገልገል ላይ የምንገኝም አለን፡፡ እኔና ሌሎች መሰል ጓደኞቼ በጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ወዳጆች ማኅበር በዛ ውስጥ ገብተን መለስተኛ የማኅበራዊ ሰራተኛ ሆነን በየፖሊስ ጣቢያ የተቋቋሙ CPU Child Protection Unity የህፃናት ጥበቃ እና እንክብካቤ ክፍል እዛ ውስጥ በቋሚ ሠራተኝነት በመስራት ላይ እንገኛለን፡፡

እንግዲህ በአገራችን ተንሰራፍቶ የሚታየው የድህነት ችግር ለመቅረፍ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ውስጥ የሚገኙትን የኅብረተሰብ ክፍሎችን የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በማድረግ ባላቸው የሙያ መስክ የድሃውን ኅብረተሰብ ማለት ነው በአላቸው የሙያ መስክ የበለጠ አሰልጥኖ ለሙያቸው አስፈላጊ የሆኑ የመገልገያ መሣሪያዎች በብድር መልክ በመስጠት የቅርብ ክትትል በማድረግ ሰዎችን ከድህነት ማውጣት ይቻላል፡፡ ይህ ሃሳብ እንግዲህ እንደመፍትሄ አድርጌ የወሰድኩት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ አሁን የምናየው ምንድነው ብዙ ድርጅቶች አሉ እነዛ ድርጅቶች የብድርና የቁጠባ ፕሮግራም አላቸው በዛ ውስጥ ብዙ እናቶችን ያሳትፋሉ፣ ድርጅቱ ደግሞ ህፃናቶችን የሚረዳ ከሆነ እነዛን ህፃናቶች የሙያ ትምህርት እየሰጠ በትክክለኛ እያስመረቀ ሰርተፍኬት እየሰጠ ብዙዎቹ በአናፂነት፣ በግንበኝነት፣ በፌሮ ሠራ ተኛ፣ በቧንቧ ሠራተኛ የሆኑ ልጆች አውቃለሁ፡፡ ከዚህ ውስጥም ከእኛ ጋር እዛው ጎዳና ላይ የነበሩና ከኛ ፕሮጀክት ወጥተው ባሌ የሚባል ድርጅት ገብተው ዛሬ እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ብዙ ወጣቶች አሉ፡፡ እንግዲህ ድህነት ስናየው በጣም አስከፊ ነው ያው ከላይ ገልጨዋለሁ ብዙ ነገር በድሃ ኅብረተሰብ ውስጥ ተፅዕኖ አለው፡፡ ስለዚህ እነዚህ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ወጣቶችና እናቶች በተለያየ የሙያ መስክ እያሠለጠኑ ከድህነት የሚወጡበትን መንገድ ቢያመቻቹ እላለሁ፡፡

*አራተኛ አቅራቢ፣ ማርታ ታደሰ*

እኔ ስሜ ማርታ ታደሰ የትውልድ ስፍራዬ አዲስ አበባ ሲሆን እድሜዬ 22 የትምህርት ደረጃዬ 12ኛ ክፍል አጠናቅቂያለሁ። የቤተሰብ ብዛት ሰባት ስንሆን ሶስት ወንድ አራት ሴት ነን። የቤተሰቤ ኑሮ ከዚህ በፊት እኛን እስኪያሳድጉን ድረስ ጥሩ የኑሮ ደረጃ ነበረን። በመጨረሻ ግን የንግዱ ስፍራ በመክሰሩ የተነሳ ድህነት ውስጥ ለመግባት ተገደናል።

አባቴ ወደ አምስተኛ ክፍል ስሆን ከችግር የተነሳ ወደ ክፍለ ሃገር በመሄድ እኛን ያስተዳድረን ነበር። እናታችን ደግሞ እዚህ ሆና ነጠላ በመቋጨት እኛን ታስተዳድረን ነበር። በእንዲህ ሁኔታ እየገፋን እያለን አባቴ ከክፍለ ሃገር በመምጣት ለእናቴ የስራ መደብ ተከራ ይቶላት እህል ነገሮችን እየነገደች አባቴ ደግሞ ከችግር የተነሳ በተለያዩ ሆቴሎች በኃላፊነት በመቀጠር እኛን እያስተማረ ያሳድገን ነበር።

ከዚያ እኔ አስረኛ ክፍል ስደርስ አባቴ እሱን እንድረዳው ብሎ እኔንና ታናሽ እህቴን በፈረቃ እንድንማር ከተደረገ በኋላ እቃ እንድንሸጥ መደብ ተከራየልን ከዛም አንዳችን ጧት ስንሆን አንዳችን ደግሞ ከሰአት እያልን 12ኛ እስክንጨርስ ድረስ እዛው ቦታ ላይ እየሰራን አባቴን እንረዳው ነበር። ከኛ በታች ያሉት ደግሞ ት/ቤት እየተከፈለላቸው ስለሆነ የሚማሩት እነሱን ለመርዳት ያንን ስራ እየሰራን እያለን ኑሮአችንን በማየት ወደ ንግዱ ልሂድ የሚል አስተሳሰብ ነበረኝ። አባቴ ግን በችግርም ቢሆን ያው እየተጣበብሽ ትምህርቱን መቀጠል አለብሽ ብሎ ዝም ብዬ 12ኛን ጨረስኩ። ልክ ከዛ እንደጨረስኩ ያንን ቦታ ያከራ ዩን ሰዎች አስለቀቁን ከዛም ሻይ ቤት ተከራይተን ከእኔ ጋር የምትሰራው እህቴ የሻይ ቤት ስራ ቀኑን ሙሉ ስለሆነ የሚሰራው የቀኑን አቋርጣ ወደ ማታ እንድትገባ ተደርጎ እዛው እየሰራች እኔ ለሁለት ሰዓት ያህል የሙያ ትምህርት እየከፈልኩ እዛው እየሰራሁ ማለት ነው ከተማርን በኋላ በአመት በአመት ማለት ነው የሙያ ትምህርቶችን ተምሬ ተመረኩ። ይሄ ሁሉ የሆነው ባለብን የኑሮ ችግር የተነሳ ነው። እንደዛ ካሳለፍን በኋላ እኔም ከተመረቅሁ በኋላ የራሴን ስራ ጥልፍ በመስራት አባቴ ስለሆነ ቤተሰብ የሚያስተዳድረው አንዳንድ ነገሮችን መርዳት ጀመርኩ። አሁንም እንደገና ታናሽ እህቴ ይሄ በዚህ እንዳለ አንድ ዓመት የሻይ ቤት ስራ እንድታቋርጥ ተደረገ እና እንደገና ከዛ ለቀን መርካቶ ተከራይተን እየሰራን እያለን እህቴ በአንድ ወቅት ላይ መክፈል አቅቷት የማታ ትምህርቱን አቆመች። በዚህ ምክንያት ማለት ነው እኔ ግን ጥልፍ እየሰራሁ አባቴን እረዳ ነበር። በእንዲህ ሁኔታ እያለሁ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመኝ ጋሻ አነስተኛ ብድር አቅራቢ የሚባል ድርጅት እዛ ሄጄ ብድር ወስጄ መጠቀም ጀመርኩ። በንግዱ ላይ የገንዘብ ችግር ስላጋጠመኝ ጋሻ ደግሞ የገንዘብ ብድር ብቻ ሳይሆን የገንዘብን አያያዝ እና ንግድን እንዴት ማስፋፋት እንዳለብኝ ስልጠና በመስጠት ጥሩ አስተዋፅኦ አድርጎልኛል። እናም እዚህ ነገር ውስጥ እንድገባ የተደረኩት ያው በችግር ምክንያት ነው ግን ችግር ባይሆርብኝ ተምሬ ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ የሚገባኝ ነበርኩ። በአጠቃላይ ድህነትን የምገልፀው በጣም ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እጥረትና ሰው መስራት እየቻለ እየፈለገ ገንዘብ ሲያጥረው ባጠቃላይ ድህነት እኔ በቤተሰቤ ውስጥ እስካየሁት ድረስ ከሰው በታች የሚያደርግ እጅግ አስከፊ ነገር እንደሆነ እገልፃ- ለሁ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ደግሞ ድህነትን ለመቅረፍና ንግድ የሚፈልጉ ሰዎችን ብድር በማበደር ንግድ እንዲጀምሩ በማድረግ እና ስራ አጥ ወጣቶችን የተለያዩ ሙያዎችን በማስተማር ደግሞ በህብረት በማሰባሰብ እራሳቸውን የሚችሉብትን ነገር ቢከፍቱላቸው ይሄን ሀሳብ አቀርባለሁ።

# ተጨማሪ ውይይት አቅራቢዎች

## *<u>አንደኛ አቅራቢ ፤ ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ</u>*

እኔ የመጣሁት ከፎረም ድርጅት ነው፡፡ ስሜ አልጋነሽ አበበ እባላለሁ፡፡ እዚህ ቀበሌ 32 ነዋሪ ነኝ፡፡ ዕድሜዬ 35 ዓመት ነው፡፡ የአምስት ልጆች እናት ነኝ፡፡ በዚህ ድርጅት ስኖር ፎረም ድርጅት ነው በድህነት የተነሳ ከየቀበሌዬ አሰባሰበኝ መዘገመኝ፡፡ ልጄ ዕጣ ወጥቶላት ነው ይሄንን ድርጅት ያገኘችው፡፡ ዕጣ ሲወጣላት ተመዘገብኩኝ ልጄን አስተማረልኝ ደብተሩን ሆነ የወር ክፍያውን ሆነ እየከፈለልኝ ችግሬን እያቃለለልኝ ሲሄድ ብድር በቡድን በቡድን እየተደራጃችሁ እየተቀናጃችሁ በማኅበር ተሰባሰቡ ተባልን፡፡ አሁን አምስት አምስት ሆነን ተደራጀን፡፡ ከተደራጀን በኋላ ቁጠባ ጀመርን፡፡ ቁጠባውን ከጀመርን በኋላ አንድ ሶስት ወር አራት ወር ከጀመርን በኋላ ብድር ውሰዱ ተባልን፡፡ የመጀመሪያዋ ተበዳሪ እኔ ነኝ፡፡ ተበደርኩ በፊት ኮርፕሬሽን ስኳር እየሸጥኩ አምስቱን ልጆቼን ሳሳድግ ነበር የወታደር ቤተሰብ ነኝ ችግር ሲያወሩት በጣም ይከብዳል ኮርፕሬሽን እያዞርኩ ምን እያልኩ ነበር ይሄ ድርጅት ፈጥኖ ደረሰልኝ፡፡ ብድሬን እየተበደርኩ በዓመት በዓመት ነው ብድራችንን የምንጨርሰው የፈለኩትን እየሰጠኝ እና ችግር መጥፎ ነው፡፡ አስቀያሚ ነው፡፡ ግን ደግሞ ያቺ ገንዘብ ስትገኝ በስነስርዓቱ አያያዝን አቆጣጠብን ገንዘብ እንዴት እንደሚያዝ ከእንግዲህ ወዲህ ደግሞ ያን ያን ሁሉ መቼም አስተምሮናል፡፡ በትንሹ በመጠኑ ችግር በጣም አስቀያሚ ነው፡፡ አሁን መንግስት ወለድ የሌለው ብድር በረዥም ጊዜ የሚከፈል ለእኛ ለድሆች ሰጥቶ እሱም ከጎናችን እኛን እየተቆጣጠረ ከወለድ ነፃ የሆነ ብር ቢሰጠን ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ወለድ ልከፍል ነው ያው መልሼ ችግር ላይ ወደኩ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የሌላው ብር በረዥም ጊዜ የሚከፈል መንግስት ደህን ቢዳስሰው ጥሩ ነው፡፡ እኔ አሁን ድርጅቱ የሚያስተምርልኝ ልጅ ትምህርቷን ልትጨርስ አንድ ዓመት ነው የቀራ ት፡፡ በጥሩ ሁኔታ እያስተማረልኝ ሳሙናም ደብተርም መመዝገቢያዋንም እየሰጠልኝ ተመስገን ጌታዬ በመጠኑም ከችግሬ ተላቅቂያለሁ እና ከዚህ በተረፈ ፎረም ድርጅት ለእኔ በበኩሌ ፈጥኖ የደረሰልኝ ችግር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ችግር በጣም ይከብዳል፡፡ ችግር ማለት አስቀያሚ ነገር ነው፡፡ እንደ ችግር ቆሻሻ ነገር የለም፡፡ ያው ደሃና ሀብታም ልክ አይመጣም፡፡ እንደ ቁሻሻ ነው የሚታየው እንደ አንድ እንደጥራጊ ነው የሚታየው፡፡ ይህን ደግሞ መንግስት የሚላቀቀውን ነገር ቢያደርግልን ከዚያ የበለጠ ደግሞ ቢያደርግልን፡፡ ከጎዳና የወጡትን ልጆች ደግሞ በድህነት ቤተሰብ አባት ወይም እናት ሞቶባቸው የወጡ አሉ፡፡ እነሱን ደግሞ አሰባስቦ አንድ የሆነ ድርጅት ከፍቶላቸው የሆነ ጥናት እያስጠና የሆነ ነገር ከፍቶላቸው ቢማሩ ጥሩ ነው፡፡

## *<u>ሁለተኛ አቅራቢ ፤ ወ/ሮ የሺ መሐመድ</u>*

ትውልዴ ወሎ ክ/ሀገር ወረሂመኑ ታዋቂ ነው፡፡ ከዛ እንደመጣሁ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ምንም ትምህርት አላገኘሁም፡፡ እስካሁን ድረስ በሰው ቤት እየሰራሁ እየኖርኩ እያለ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ሴት ልጅ ወለድኩ፡፡ በዚያ ኑሮ እያለሁ ወደ ዘመድ ተጠግቼ ልጄን በማሳደግ ላይ እያለሁ ችግሬ በጣም እየገፋብኝ ሄደ፡፡ በዘመዶቼ ላይ ሆኜ ልጄን እያሳደኩኝ ኑሮ በጣም አስቸጋሪ ሆነብኝ፡፡ ችግሩ እየባሰብኝ በጉልበት ስራ ልጄን እያሳደኩ ወደ ቅጠል መልቀም ሰው ቤት እንጀራ መጋገር ጀመርኩ፡፡ ዘመዶቼ ያለፍላጎቴ ለሌላ ሰው ዳሩኝ፤ በዛው ሁለተኛ ልጄን ወለድኩ፡፡ እሱም አልሆነም፡፡ በዛው ላይ ደግሞ እኔም ኑሮዬ እንደዚህ እያልኩ ስኖር ድጋሚ አረገዝኩ፡፡ ያንን ልጅ ወለድኩ፡፡ ችግሩም ተጫጫነብኝ፡፡ ሁለተኛ ለረዥም ጊዜ በጥገኝነት ከዘመዶቼ ጋር እያለሁ እነሱም ኑሯ ቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ውጪ ወደቀድሞ ስራሽ ተመለሺ ልጅ ነሽ ልጆቹም ወደ ገጠር ይሂዱና ይኑሩ እኔ ቀደም ሲል ከገጠር ወጥቼ አዲስ አበባ ስኖር ትምህርት አልተማረኩም ልጆቼን አስተምራ ለሁ እኔ ተመልሼ ወደ ገጠር እንኳ አልሄድም ልጆቼንም አልወስድም በማለት ልጆቼን ይዤ ከዛች ቤት ሲያስወጡኝ ከዘመዶቼ ጥገኝነት ወጥቼ እንዲህ ትንሽ ሰርቼ ባገኘሁት ልጆቼን እያስተማርኩ እቤትም ወዲያ ወዲህ ስል ስቸገር ቀበሌ መስተዳድር ባለቀስኩበት ሰአት አሁን ቤት የለንም እነዚህን ልጆች ይዘሽ የት ልትወድቂ ነው አሉኝ፡፡ ያለኝን ቀደም ብዬ በየሰው ቤት ሰርቼ እንጀራም ጋግሬ ባለኝ ገንዘብ ያቺን እየሸጥኩ ለትንሽ ጊዜ የቤት ኪራዬን ከፍዬ ኖርኩ፡፡ ልቋቋመውም አልቻልኩም፡፡ ስላልቻልኩ ወደ ቀበሌ መስተዳድር ሄጄ ልቅሶዬን አሰማሁ፡፡ እሺ እንሰጥሻለን አንቺም በቆራጥነት ልጆቹን አስተምራ ለሁ ብለሻል እንሰጥሻለን አሉኝ፡፡ ቀደም ሲል ያቺን ቤት አገኘሁ፡፡ ለነገሩ ግድግዳው ገጠምጠም ብሎ ጣሪያዋ ሰማይ ያሳያል፡፡ ያቺን ቤት እሺ ብዬ ገባሁ፡፡ ምንም ነገር የለኝም፡፡ ልጆቼና እኔ ሶስት ሆነን እዛች ቤት ገባሁ፡፡ እዛች ቤት ስገባ እራት የለኝም ቀኑን ሙሉ ጫካ እውላለሁ፡፡ ከጫካ ተመልሼ ለልጆቼ ባገኘሁት ስንውልም ስናድርም እግዚአብሄር ይመስገን መቼም በኛ በባህላችን ጤና ከሰጠው የሰው ልጅ ሰርቶ ያገኛል፡፡ ሰው ቤት እንጀራ ጋገራ እየጋገርኩ ምን እያልኩ ልጆቼን ትምህርት አስተምራቸዋለሁ፡፡ እቤት አይ- ውሉም፡፡ አላማዬ ልጆቼን ለማስተማር ስለሆነ እኔ

ስላልተማርኩ በጣም ስለሚቆጨኝ ልጆቼን እያስተማርኩ እያለሁ አሁን ዝናብ የጣለ ጊዜ አነስ ያለው ልጄ ውይ እዚህ ቤት ከመኖር እደጅ ይሻለኛል ለምንድነው እንዲህ የምታደርጊው ግድግዳው ብቻ ተገጣጥሞ ጣሪያው ይታያል፡፡ እንዴ ዝናቡ እኮ ጨፈጨፈን ይለኛል ላስቲክ ገዛሁና ያችን ላስቲክ በላያችን ጠለል አድርጌ ልክ እንደዛው ጎርፍ እንዳሚወርድ በባልዴ እየደቀንኩ እደፋዋለው፡፡ አሁን ትንሽ ትንሽ ለሶስት ዐመት እንዲህ እያልኩ ኖርኩ፡፡

አንድ ቀን እንደተኛን የማስታውሰው ግድግዳው ፍንቅል አለ፡፡ ልጄ እንደተኛች በላዬዋ ላይ ሊወድቅብኝ ሲል ውይ ተነሽ ስል ተናደ በተናደበት ሰአት ላይ ጠዋት ተነሳሁና ወደ ቀበሌ መስተዳድር ሄድኩ፡፡ ይህች የሰጣችሁኝ ቤት ዝናብ አፈረሰብኝ ለመስራትም አልቻልኩም እንግዲህ ልጆቼን ይገፉ እንዴት ላድርግ ስላቸው መጡና አዩልኝ፡፡ እኛማ መስራት አንችልም፡፡ እንግዲህ እግዚአብሄር ይርዳሽ ሰውንም ሰፈሩንም ለማምኚና ይህችን ግድግዳዋን እንደምንም አድርጊ አሉኝ፡፡ አይ እኔማ እንደዛ አላደርግም፡፡ ማነው እሺ የሚለኝ አልኩና የዕለት ጉሮሮዬ አለች እሷን ወዲያ ወዲህ እያልኩ በአሰብኩበት ሰአት ክረምት ስለሆነ መስከረም ላይ አስታውሳለሁ 1990 አኮርድ ኢትዮጵያ የሚባል ድርጅት መጣና በሴቶች ዕድር እንዳቅሜ የወንድም የሴትም ዕድር አለኝ፡፡ ተሰባሰ-ቡና እስቲ አኮርድ ኢትዮጵያ የሚባል መጥቷል ተሰባሰቡና ገንዘብና ቁጠባ ይሰጣልና የሺ ለአንቺም ይጠቅምሻል ይህችን የፈረሰች ቤት ትሰሪባታለሽ፣ ጎበዝ በርቺ አሉኝ፡፡ አይ ይሆን? እሺ ብዬ ተሰባሰበን ለመጀመሪያ ጊዜ ቁጠባውን ተሰባስበን ትንሽ ገንዘብ አገኘን፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ለእኔ ብድር ሰጡኝ፡፡ ይህች ሙከራና ናትና ቤቷን አንሰራበትም ነገር ግን ላስቲክ ገዛዛሁና በሳጠራ ክልል አድርጌ ትንሽ ጊዜ አሳለፍኩ፡፡ ያቺን ወደ ሐምሌ ጨረስኩና ሌላ ብድር ወሰድኩ፡፡ እሷንም እንዲህ ስሰራ አይ አሁንማ ክረምቱ ሊያፈርስብኝ ነው ይቺን ነገር መስራት አለብኝ ቅድሚያ ትንሽ ጠዋት ጠዋት ለቁርስ ዳቦ እጋግራለሁ፡፡ ችግሩ ውሃ ላይ ነኝ ያለሁት፡፡ ቶሎ ቶሎ ይቺን ቤት እስከ ማዕድቤቴ ማፀዳዳት አለብኝ ብዬ በተሰጠኝ ገንዘብ ማኅበርተኞቼን ብድር እና ቁጠባ ጠየኳቸው፡፡ አሁን ይሄ ገንዘብ የሚመለስ ነው ግን ገንዘቡ ተመላሽ ሆኖ አንቺ ይቺን ቤት በርትተሽ ብትጠጋግኚ ጥሩ ነው፡፡ በርቺ ብለው አበረታቱኝ፡፡ ያቺን ቤት ከዛም እንደምንም በአንደኛው ቆርቆሮዋን እንደምንም ብዬ በአንድ ጊዜ ሰራርቼ በሶስት ቀን እግዚአብሄር ይመስገን ቤቷን ጣሪያዋንም ግድግዳዋንም አቋቁሜ ተመስገን አሁን ደህና ናት ቤቷ፡፡

እና ይሄ አኮርድ ኢትዮጵያ እኛ ችግርተኞችን ያለብንን ስቃይና ችግር በመረዳት እሱ ከመጣ እግዚአብሄር ይመስገን ጤፍም እየሸመትኩኝ እንጀራ እየጋገርኩ እንደገናም ከዛች ችግር ትንሽ ተሻሽዬ በጣም ከበፊቱ አሁን ተመስገን ደህና ነኝ እላለሁ፡፡ ከእኔ በታች ደግሞ ያሉ አሉ ስለዚህ አላማዬ ልጆቼን ማስተማር ስለሆነ ልጆቼም እየተማሩ ክፍያም ቢሆን እየከፈልኩ ሴቷ ልጄ አሁን 11ኛ ክፍል ናት፡፡ በሚቀጥለው ነው የመትጨርሰው፡፡ ክፍያውንም እየከፈልኩ በዚችው በማገኛት ላይ አትርፌ በማገኛት ላይ ደብተሩን ምኑን ምኑን እራሴ ነኝ የማሟላው፡፡ ዕድርንም ሆነ ሁሉንም ነገር፡፡ እግዚአብሄር ይመስገን ጤና ከሰጠኝ ልጆቼም እኔም ተመስገን እየሰራሁ ነው አሁን፡፡ ደግሞ ይሄ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለእንደኛ ያሉ ድሃዎች ለእንደኛ አይነት አሰቃቂ ኑሮ ለምንኖረው ዝናቡም ፀሀዩም ረሀቡም ከሚደራረብ ሁሉም ያው ማለት ነው በበረንዳ ተዳዳሪዎችም ቤትም ተብሎ በምንኖረው ችግር ካለ ያው በጣም አሰቃቂ ነው ብዬ ነው በበኩሌ የሚሰማኝ፡፡ ደግሞ እንደዚህ አይነት ድርጅትም ሲረዳ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡ ችግራችን እየተሻሻለ እየተቀረፈ ነው፡፡ እግዚአብሄረ ይመስገን ይህ ድርጅት ባይመጣ ኖሮ ትምህርትንም ሆነ ሁሉንም ያሰብኩትን ዐላማ ለማሳካት በጣም ይከብደኝ ነበር ብዬ ነው የማስበው፡፡ ወደፊትም ያለውን ዕርዳታ ለእንደኛ አይነቶች ችግረኞች ችግራቸውን ቢቀረፉላቸው ጥሩ ነው ብዬ ነው የማስተላልፈው መልዕክት፡፡

# አጠቃላይ ውይይት

<u>*ጥያቄና መልስ*</u>

1. አሁን ከሁሉም ከሰማናቸው ሰዎች ከችግር የወጡት ከNGO እርዳታ የብድር አገልግሎት በማግኘታቸው ነው ራሳቸውን ሊያሻሽሉ የቻሉት። እነሱ ከራሳቸው ልምድ (ኤክስፔሪያንሳቸውንና) ተሞክሯቸውን የገለፁት። ነገር ግን እኔ ደግሞ ሌላ ልጠይቃቸው የምፈልገው ከአካባቢያቸው በራሳቸው ደግሞ ዕርዳታ ሳይጨመርላቸው ራሳቸው አንዳንድ ጥረቶች በማድረግ የተሻሻሉ ሰዎች ካሉ እናንተ ብትነግሩኝ ደስ ይሰኛል።
2. ሁሉም ችግርን እንደገለፁት አስቸጋሪ ነገር ነው በሚል ነው ያለፉት። ለመሆኑ እንዲያው የእነሱ እይታና ባሳለፉት ህይወት ድህነት ማለት ምን ማለት ነው። ይህን ለመስማት ፈልጌ ነው። እና እንዴት ነው ድህነትን የሚያዩት?
3. እኔ እንኳን ከአቅራቢዎቹ ምንም ዓይነት ስለ ድህነት ማብራሪያ የምፈልገው የለኝም። ግልፅ ያደረጉት ይመስለኛል። በተለያዩ የህይወት መስክ አዲስ አበባችን ውስጥ ድህነትን ሁላችንም የምናየው ይመስለኛል። እናም ብዙም ማብራሪያ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሆኖም ግን አንድ ስጋት አለኝ። ዛሬ እዚህ መድረክ ላይ የምናያቸው ሰዎች ስለድህነት የተለያዩ መልክ የተናገሩ ሰዎች እንዲያው ከፋም አማረም በጣም ከባሰበት ሻል ያሉ ወይም የተወሰነ ዕርዳታ ያገኙ በመጠኑም ቢሆን አጥጋቢም ባይሆን የሆነ ዕርዳታ ያገኙ ይመስለኛል። እንግዲህ ይሄ አንድ የሚያነሳው ጥያቄ ያለ ይመስለኛል። እነዚህ NGO ድርጅቶችና መንግስታዊ የሆኑ ድርጅቶች በአዲስ አበባ ውስጥ ያለውን ድህነት እነዚህ ሰዎች እዚህ አሁን ሲናገሩ የሰማናቸውን ያህል ለመርዳት ችሏል ወይ ችግሩንስ በምን መጠን ቀረፈውታል? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ይሰማኛል። እዚህ መድረክ ካየናቸው በባሰ ሁኔታ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ያሉ ይመስለኛል እናም ያሉት ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ይሄንን ችግር በሙሉ ሸፍነውታል ለማለት ትንሽ የሚያስቸግር ይመስለኛል። አንዱ እንግዲህ ካለውም የችግር ስፋት ካለውም NGOና መንግስታዊ የሆኑ ድርጅቶች ከአቅም ማነስ አንፃር ሊሆን ይችላል ወይም የፍላጎት ማነስም ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ችግሮች ሊመጡ ይችላሉ። አንድ ቁልፍ የሆነ ነገር ብዙ ትኩረት ያልተሰጠበት የሚመስለኝ በዋናው መሰረታዊ መፍትሄ ለድህነት የራስ ታታሪነት ይመስለኛል መፍትሄ ሊመጣ የሚችለው ከደሃው ከራሱ ነው። እርግጥ እገዛ ያስፈልገዋል። ግን ብዙ መመልከት ያለብን ወደራሳችን እንጂ ወደ ውጪ ብቻ መሆን የለበትም። በተወሰነ ደረጃ ማርታ ባቀረበችው ላይ ይህንን ሁኔታ አይቻለሁ። ለምሳሌ አባቷ ያ ችግር በደረሰ ጊዜ ከከተማ ወደ ገጠር ሄደው እነሱን ለማደራጀት ያደረጉት አንድ ዓይነት ጥረት አለ። ያ ጥረት በሁሉም መሰረታዊና ቁልፍ መፍትሄ ይመስለኛል። ይሄን አካሄድ እንዴት እንደሚመለከቱት ሌሎች አላውቅም። አስተያየት ቢሰጡበት?
4. የመጣሁት ከተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ነው። ግርማ ኃይሉ እባላለሁ። ከዚህ ቀጥዬ ደግሞ ይህን መድረክ ላዘጋጁት ያለኝን የከበረ ምስጋና መግለፅ እንፈልጋለን።

የምንችለውን ነገር እንግዲህ በየደረጃው ለማድረስ እንሞክራለን። የሚቀጥለው ነገር ግን ምንድነው? አሁን ተናጋሪዎች በእነሱ ግምት የሰጡን መረጃ አለ። ምን አልባት የሚሻለው የሚመስለኝ እንደሚመስለኝ ይሄ መድረክ ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? ደሃ ማነው? የሚለውን ዓይነት አስተሳሰብ አንድ እይታ መመዘኛዎች ወይም አንድ ዓይነት አመልካች ነገሮች ላይ ለመስማማት ወይም ለስራ እንዲያግዙ አንዳንድ ኢንዲኬተር ማሰብ ይረዳል ይሆን ወይ የሚል ግምት አድሮብኝ ነው የተቀበልኩት። ለምሳሌ ሀገሮች እነ እከሌ እከሌ ሀገሮች ድሆች ናቸው ይባላል። እነዚህ ሀገሮች ድህነታቸው የሚመዘንበት አንዳንድ ምልክቶች አሉ። ከዛ አኳያ ነው ድህነት በሀገር ደረጃ ምን ዓይነት መመዘኛና ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላል። ከዚህ ጋር አከታትዬ አንዳንድ ነገር የሚመስለን የሰው ልጆች ፍላጎት ማሚላት የማይቻልበት ሁኔታ ካለ ይህ ድህነት የሚባለውን ነገር ማየት ይቻላል። እንዲህ አይነቱን ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? ድሃ ማነው? የሚለውን ብናይ ለወደፊት አሰራር የሚሻል ነው የሚል ግምት አለኝ በዚህ መንገድ ይሄ መድረክ ቢቀጥልና እነሱ እንደገና ያቀረቡትን ነገር መልሶ ከመጠየቅ ምንአልባት ለወደፊቱ ግን የሌሎች ሰዎችን ልምድን ከመስማት ይልቅ ምንድነው ድህነት? ደሃስ ማነው? በኢትዮጵያ የኑሮ ሁኔታ ምን ዓይነቱን መመዘኛ ማየት ብንችል የሚያግዝ ነው የሚመስለኝ።

*መልስ ከወ/ሪት ሰናይት ዜናዊ*

ሁለት ጥያቄዎች ይዣለሁ።

1. በራሳቸው አነሳሽነት ከድህነት ስለተላቀቁ ሰዎች እና
2. ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? ሲሆኑ፣

    1. በራሳቸው አነሳሽነት ከድህነት የተላቀቁ ድሆች እኔ በሰፈሬ ያየሁት አለ። አሁን ባለ እስፔር ፓርት እና ባለብዙ ንብረት ነው። ማለት ስንጀምር ንግዱን እኩል ነው የጀመርነው። እኔ ልብስ አጥቤ በማገኛት ድንች ነበር የምነግደው። እኩል ነበር የጀመርነው ድንች ነግዶ እንደኔ ቤተሰቡን ማስተዳደር ስለነበረበት ድንች ቀቅለን እኩል ነበር የምናወጣው አንድም ሰፈር ነበርን እኔ የማገኛትን ብር አጠራቅማለሁ እሱም ያጠራቅማል እኩል እቁብ እንጥል ነበር። ሰፈሬ ውስጥ ጉልት ያላቸው ሰዎች ድንች የሚሸጡ በምናገኛት ብር እቁብ በጋራ እንጥል ነበር። እኔ ባጋጣሚ እናትና አባቴ ሲታመሙ ያጠራቀምኩትን ብር ለዛ አጠፋሁት። እሱ ግን ባጠራቀማትና በጣለባት አየር ባየር ንግድ ከስፔርፓርት ወደ ስፔር ፓርት ጀመረ። ከዛም አድጎ ባለ ትልቅ ስፔርፓርትና የኤሌክትሪክ መሸጫ ቤት ተከራይቶ የሁለትና የሶስት ስፔርፓርት ባለቤት ለመሆን በቅቷል። ይህንንም አይቻለሁ በራሱ ተነሳሽነት ማለት ነው። አምስት ሳንቲምም ቢሆን ያለምንም ምክንያት ሳያወጣ ቤተሰቦቹን እየረዳ ለቁም ነገር የደረሰ ልጅ አውቃለሁ።

    2. ድህነት ማለት ግን በጣም አስከፊ አስጠሊታ ከሰው በታች የሚያደርግ ነው። ቀደም ሲልም ተናግሬዋለሁ። ጎረቤቶቼ ከእኔ ጋር በልተው አብረውኝ ያደጉ ሰዎች አባቴ ጡረታ ከወጣ በኋላ በቤታችን ሁኔታችን በአንድ ወቅት የምንጠጣው ውሃ ያጣንበት ጊዜ አለ። እንደዛ ሆነን ሲያዩ የጠሉን ሊጠጉን ያልፈለጉ ያስጠላናቸው ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ ድህነት ማለት በጣም የሚያስጠላ ኑሮ ማለት ነው። ይህን ግን ጎበዝ የሆነ ሰው ታታሪ ሰው መወጣት ይችላል። ባለው አቅምና ጉልበት ከሰራ ድህነትን ማሸነፍ ይችላል። ግን ድህነት ማለት በጣም አስጠሊታ ከሰው በታች የሚያደርግ ደሃ ከሆነ ማንም አያምነውም አብሮት የበላ ሰው ሲቸገር ቢያየው አምስት ሳንቲም አበድረኝ ቢለው የሚያበድረው የለም። ድህነት ማለት እንደዚያ የሚያደርግ ነው። እናም በጣም አስቀያሚ ነገር ነው።

*የግዛቸው ኃይሌ መልስ*

1. አንድ ሰው ብቻውን አለምንም አጋዥ ከድህነት እንዴት ሊወጣ ይችላል?
2. ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? የሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች ለመመለስ እሞክራለሁ።

    1. በእርግጥ በአንድ እጅ ማጨብጨብ አይቻልም። አንድ ሰው ብቻውን ያለበትን የቤተሰብ ኃላፊነት ተማሪ ከሆነ ትምህርቱን ለመቀጠል ቤተሰቡንም ለመርዳት ያለው የኑሮ ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ግን በአጋጣሚ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ድርጅቶችን ሳይጠይቅ ኅብረተሰቡን ሳያስቸግር በእውነት ቻንስ ልበለው በዚህ መልኩ ከድህነት ሊላቀቅ ይችላል። ነገር ግን በብቸኝነት ኑሮ የማለፉ ሁኔታ አይገኝም ወይም አይታይም። እናም ሬር ነው።

    2. ስለድህነት ከምንም በላይ ተስፋ የመ-ቁረጥና ከአሁን በኋላ እኔ ሰው እሆናለሁ የሚለውን አስተሳሰብ ከአንደበቱ ያመ-ነጫል። ከማኅበራዊ ኑሮ እራሱን በራሱ በፈቃደኝነት ያገላል። ይህ በዚህ ብቻ ሳይበቃው ራሱን በራሱ ከአካባቢው ለመሰወር ይገደዳል። እንደውም በድህነት ምክንያት የሚለምኑ ሰዎች አሉ። ይሄንንም የአካባቢው ሰዎች እንዳያዩዋቸው ራቅ ወዳለ ስፍራ ሄደው በልመና ይሰማራ ሉ። ዋናው ችግሩ ግን በዛው መቀጠሉ ነው። ደሃው ማነው የሚለውን ደግሞ ስንመለከት ደሀው ማን እንደሆነ ለማወቅ ይከብዳል። ግን ደሃ መሆኑን የሚመሰክርለት ኑሮው ነው። ሌላው ከማኅበራዊው ኑሮ ከተገለለ እቁብ ከሚባል፣ ዕድር ከሚባለው ሌሎችም ከማኅበራዊ ኑሮዎች ከተገለለና ካልቻለ አቅም ካነሰው እንዲሁም የምግብ ፍላጎት ኖሮት ይህንን ካልተሟላለት የጤና የሀ-ክምና ሌላም የዕውቀት ወይም የትምህርት ዕድል ማግኘት ካልቻለ ደሀ ማለት ይሄ ነው። ሌላ ምን ደሃ አለ። በድህነቱ ምክንያት ይህንን ሁሉ ማጣቱ በሌላ ደካማ በሆኑ በሽታዎችን መቋቋም ሳይችል እራሱን ለመጨረሻው ጊዜ አሳልፎ የሚሰጥ ማለት ነው።

*የወ/ሪት ማርታ መልስ*

1. እኔ የምናገረው አንድ ሰው ከብድር ሌላ በራሱ ጥረት ድህነት ማሸነፍ ይችላል ወይ

የሚለውን ነው:: ለዚህም መልሴ አዎ ነው የምለው:: እኔ አባቴን ባየሁበት ሁኔታ ማለት ነው:: ድህነት ባጋጠመን ጊዜ ቶሎ ወደ መረታት መውደቅ አልሄድንም:: በራሱ ጥረት ከሰው ጋር በመቀጠር ከዚያም ያንን ትቶ ደግሞ ትንንሽ ሻይ ቤቶችን በመከራየት በቃ በትዕግስት ማለት ነው አሁን በደህና ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት ነው አባቴ:: እና ድህነትን በራስ ጥረት መወጣት ይቻላል ማለት ነው::

2. ያው ድህነት ማለት ደግሞ ቅድም ጠቅሸዋለሁ:: ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እጥረትና ከሰው በታች የሚያደርግ ነገር ነው::

*<u>የወጣት ሲሳይ ገሰሰ መልስ</u>*

እኔ እነዚህ ጉዳዮችን የማየው በድርጅት የሚታቀፉና በሌላ ሰዎች የምክር አገልግሎት ታክሎበት ራሳቸውን ያሻሻሉ በሚል ነው::

እኔ በሁለት ነገር ነው የማየው ያልኩት ለዚህ ነው:: አሁን ከኔ ጋር የነበሩ ልጆች እዛ ድርጅት ውስጥ አንድ ላይ ታቅፈን እዛው ስልጠና አግኝተን እራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ተብለው በግሩፕ ተደልድለው እራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ የቀበሌ አዳራሽ ተፈቅዶላቸው እራሳቸውን እንዲያሻሽሉ የተመደቡ ልጆች አሉ:: ግን እነዚህ ልጆች ጥሩ አካሄድ ሄደው ሲያበቁ በመጨረሻ ላይ አንደኛ ከሱሳቸው ማለትም ከሲጋረ ከጫት ሊላቀቁ ያልቻሉ አሉ:: እና እርግጠኛ ነኝ ከምንም ነገር ነፃ ነኝ ማለት እችላለሁ:: እንዲህ ስል ግን ከአንዳንድ ሰዎች ወጣት ሆኖ እንዴት ከሱስ ነፃ ሊሆን ይችላል ይላሉ:: እኔ ያለፍኩበት ስለሆነ ሲጋራ ማጨስም ጫትም ብቅም የማውቀው ነገር ስለነበረ ለእኔ አዲስ አይደለም:: ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የሱስ ተገዢ አይደለሁም:: ስሜቱም የለኝም ያንን ወደፊትም አላደርገውም:: እና ምንድነው እኔን የመሰሉ ጓደኞቼ አንድ ላይ ኖረን በአንድ ላይ በድርጅት ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት ተካፍለን እስካሁን ጎዳና ላይ ያሉ አሉ:: የሞቱም አሉ:: አገልግሎቱን ግን እኩል ነው ያገኘነው:: ትልቁ ነገር ምንድነው ሰው የሚሉትን የሚመክሩትን በደንብ መስማት አለበት:: ሁለተኛ ደግሞ የራስ አነሳሽነት መኖር አለበት:: እኔ ለዚህ ልጅ ነኝ:: በእርግጥ እስካሁን አዕምሮዬ ውስጥ ያልወጣ አለ:: አባታችን በሞተ በአርባኛው ቀን እቤት ውስጥ የነበሩ ወርቅም ተሸጠ ልብስም ተሸጠ ቁምሳጥንም ተሸጠ ብዙ ነገርም ተሸጠ:: ከአቅማችን በላይ ሲሆን ነው እኔም የወጣሁት:: ጎረቤት ያሉት ግን ምን ይላሉ የዕከሌ ልጆች ስለወጡ ልብሱን ጠብቁ እንዳይወስዱ ተጠንቀቁ ገቡ፣ ወጡ የተሰጣ ልብስ ንብረት ደጅ ካለ እኛ ከዛ ቤት ስንወጣ በአይነ ቁራኛ ነበር የምንጠበቀው:: ገና ለገና አባታችን ስለሞተ ይሄ ነገር አዕምሮዬ ውስጥ ገብቶ ዛሬ ለዚህ አበቃኝ:: እንዳዚህ ብለውኝ ጎዳና ላይ ሰርቼ ያ ነገር ያጋጥመኛል ብዬ አልጠበኩም፣ ጎዳና ተዳዳሪ እሆናለሁ፣ ሲጋራ አጨሳለሁ እቅማለሁ የሚል ፍላጎት አልነበረብኝም:: በኋላ ላይ ግን አሸንፎ ከተተኝ በድጋሚ እነዚህን ነገሮች ስላገኘሁ የምክር አገስግሎት አለ:: በራሴ አነሳሽነት ለአዕምሮዬ ጥሩ ነገር አሳስበዋለሁ እናም ለዚህ በቅቻለሁ::

በራስ አነሳሽነትን በሁለት ነው የምናየው:: አንድም በራሳቸው ተነሳስተው፣ አሊያም በድርጅት ድጋፍ ተደርጎላቸው ራሳቸውን ያሻሻሉ:: ሌላው ድህነት ማለት በጣም አፀያፊ ነው:: እኔ እስካሁን ድህነት ሲባል ትዝ የሚለኝ እኛ ቤት አባታችን እያለ ዶሮ ይታረዳል፣ በግ ይታረዳል፣ ቅርጫ ይገባል:: አባታችን ከሞተ በኋላ ግን እኛም ልጆች ነን ከእኔ በታች ያሉም ህፃናቶች ናቸው:: እኔ የ14 አመት ልጅ ሆኜ ነው የወጣሁት:: ከዚያ በታች ታናናሾቼ አሉ:: ራበን ምግብ የለም አያውቁም:: ሲርባቸው ራበን ነው:: እናም እናቴ ከየት ታምጣው በተለይ አመት በዐል ሲሆን:: እኔ አስታውሳለሁ ጥላን የሄደችበት ጊዜ አለ:: እንግዲህ ድህነት ይህን ያህል አስከፊ ነው:: ልጆችን ያስጥላል፣ ቤተሰብን ይበትናል፣ ቅድም ገልጬዋለሁ እንግዲህ ድህነትን ደግሞ በዚህ መልኩ እናየዋለን::

*ሁለተኛ ዙር ውይይት*

1. ድህነት ምንድነው? ደሀስ ማነው? ተብሎ ሲጠየቅ ስምቻለሁ:: ነገር ገን እንግዶቹ (ተናጋሪዎቹ) በደንብ ያስቀመጡት ይመስለኛል:: ድህነት ምንድነው? ማነው ደሀ? የሚለው ብዙ ጥናት የሚያስፈልገው አይመ-ስለኝም:: በጠቅላላ ዙሪያችን ያለው እሱ ስለሆነ እናውቀዋለን:: ነገር ግን እኔ ለማንሳት የምፈልገው አሁን ድህነት ምንድነው? ማነው ደሀ? የሚለውን ሳይሆን በመጀመሪያ ደረጃ መሰረታዊ መንስዔ የድህነታችን (የድህነቱ) መሰረታዊ መንስኤ ምንድነው? ያንን ማወቅ ይመስለኛል ዋናው ጉዳይ ከዚያ በመነሳት ወደመፍትሄ ለመሄድ የሚቻል ይመስለኛል:: በአጠቃላይ ድህነት ያልነውን በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል:: ድህነት መሰረታዊ ፍላጎቶች በትንሹ የመኖር የምግብ፣ የልብስና የመጠለያ የመሳሰሉ መሰረታዊ ነገሮች ያልተሟሉለት ዜጋ ደሀ ነው:: ከዛ ወደሚቀጥለው ይሄዳል:: በአጠቃላይ ሳየው እነዚህ ችግሩን ለመቅረፍ በተናጥል የሚደረጉ ሙከራዎች ይመሰገናሉ:: ነገር ግን ሳየው ችግሩ እየባሰ ይሄዳል እንጂ የመቀረፉ ሁኔታ አይታይም:: እንደዚህ በተነጣጠለ መልኩ ሰፋ ባለ መልኩ ይሄ የኢትዮጵያ ጠቅላላ ህዝብ ከትንሽ እስከ ትልቅ ድረስ የሚረባረቡበት አንድ አይነትም ፈንድ ሊሆን ይችላል፣ ትንሽ በትንሽ ብትወረውር ብዙ ሊሆን ስለሚችል አንድ እንዲህ ዓይነት ነገር ቢታሰብ ብዙ ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች ሙከራ ያደርጋሉ:: ነገር ግን ምንም ጠብ አይልም ይሄ ነው:: የሚያሳስበው ከዚያ በበለጠ በአገር ደረጃ በመንግስት ደረጃ ከፍተኛ መረባረብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል::

   ሌላው ለምሳሌ ትምህርት ተነስቷል ጤናም ተነስቷል:: ማንኛውም ዜጋ ምን አልባት ትምህርት ነፃ ነው:: ሀገራችን ግን ለሁሉም የሚዳረስበት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ገንዘብ በማጣት ከትምህርት ገበታ በተለይ ከፕራ ይመሪ ኢዱኬሽን መገለል ያለበት አይመ-ስለኝም:: ለዚህ ብዙ በጀት በልዩ ጉዳይ ይወጣል:: ለዚህ ከፍተኛ ዘመቻ ያስፈልገዋል:: መንግስት ለዚህ ከፍተኛ በጀት መመደብ ያለበት ይመስለኛል:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሰረታዊ ትምህርትን ማግኘት ያለበት ይመስለኛል:: ደሀም ሆነ ሀብታም ሀብታም፣ በራሱ እየከፈለ ያስተምራል:: ነገር ግን ማንኛውም ዜጋ ለዚህ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልግ ይመስለኛል::

   በመጀመሪያ ቅድም ተናጋሪዎቹ እንዳሉት ሁሉ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በዛሬው ዕለት የጉዳዩን ባለቤቶች እዚህ አምጥቶ ስላወያየ በጣም ማመስገን እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም በተለምዶ ምሁራን ተገናኝተው ስለሶስተኛው ወገን መነጋገር በሚጀምሩበት ጊዜ የሚሆነው ነገር ቢኖር ወይ ከመፅሀፍ ከተገኙ መረጃዎች ላይ ተመርኩዘው የሚሆን ነው:: አለበለዚያ ድህነትን በትዝታ በማስታወስ ሊሆን ይችላል ድህነትን የሚያወሩት:: ያ ማለት ዛሬ ቁስሉ ሽሮ ህመሙ በማይሰማበት ሁኔታ ላይ እንደገና እንነጋገር ቢባል ብዙ ሰርጎ የሚገባ መልዕክት ማስተላለፍ አይቻልም:: ስለዚህ ይሄ ነገር እንደዚሁ እንዲቀጥል ለማሳሰብ ነው:: ሁለተኛ ቅድም እንደተባለው ድህነት ቁሳዊና መንፈሳዊ እጦት ነው:: ቁሳዊ እጦት በምንልበት ጊዜ የመብት እጦት ነው:: ሰርቶ የመኖር እጦት ነው:: ሰብአዊ መብት መገፈፍም ማለት ነው:: ከዚህ አኳያ እንግዲህ ችሮታን መፈለግ ማለት ደግሞ አይደለም:: ደሀ እንግዲህ ቅድም እንደተባለው ጤናውን ከሰጠው ሰርቶ መኖር ይችላል:: ሰርቶ ማግኘት ይችላል:: ከዚህ ጋር እንደ ስንቅ ትቼ መሄድ የፈለኩት መድረኩን የፈለኩበት የገንዘብ ብድር አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ከወለድ ነፃ መሆኑን በጉጉት የምንፈልገው መሆን የለበትም:: በአጭሩ ይህንን አዳራሽ ግሎባል በነፃ ቢሰጠን ኖሮ ዝም ብለን አንወጣም:: ቢያንስ ማፅጃ መጥረጊያ መግዣ ወይም እንዲያፀዳው የሚያስፈልገውን የጉልበት ዋጋ ከፍለን ነው የምንወጣው:: የተገለገልንበት ነውና:: ገንዘብን የሚያክል ነገር ሲመቻችልን ደግሞ የገንዘቡ ክራይ መከፈል ይኖርበታል:: የገንዘቡ ኪራይ ምንድነው? አንደኛ የተሰጠውን ገንዘብ ውሎ ባደረ ጊዜ አቅሙ እየደከመ ስለሚሄድ የዛሬ ዓመት የነበረው የአንድ ብር ዋጋ ዛሬ ስንት ነው? ነው ጥያቄው:: ሁለተኛ ያ ገንዘብ እያደገ በሄደ ቁጥር መልሰን መላልሰን የመንጠቀምበት በመሆኑ ወለድን ልንፈራው አይገባም:: ወለድን ከፈራን ችሮታን ነው የምንፈልገው ማለት ነው:: ተመፅዋችነትን ነው ማለት ነው የምንፈልገው:: እኛም ምናልባት ከወለድ ጋር የተገናኘውን ነገር እንደው ዝም ብዬ እንዳልሄድ ነው በዋነኝነት የጠየኩት መድረኩን:: በጣም አመሰግናለሁ::

2. እኔ በአጭሩ አስተያየት ለመስጠት የፈለኩበት ነጥብ ከመድረክም ሆነ እዚህም መካከላችን ከሚገኙ እህቶታችን ከተሰጠው ማብራሪያ እኔ በግሌ ለመረዳት የቻልኩት አንዱ ለድህነት መሰረት መስፋፋት የቤተሰብ ቁጥር መብዛት ይመስለኛል ወይም እነዚህ ወጣቶች ራሳቸውን ችለው እንዲሁ ማደግ ሲችሉ የሌላ የወንድሞቻቸውን የእህቶቻቸውን ችግር ለመቅረፍ ባደረጉት ርብርብ ደስተኛም

ናቸው፡፡ ውጤታማም ሆነዋል፡፡ ነገር ግን የተሻሉ ሊሆኑ ይችሉም ነበር፡፡ ይሄ ለምን ሆነ ሲባል ሌላ መለስ ብለን ማሰብ ያለብን የሀገራችን የድህነት ችግር ከህዝብ ቁጥር ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የህዝብን ቁጥር መቀነስ አንዱ የድህነት መቀነስ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ አዘጋጆች በዚህ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ላይ በጥብቅ ልንወያይበት የሚገባው ወይም መገታት ያለበት የህዝብ ቁጥር ቅነሳ ወይም ከእድገት ጋር የተመጣጠነ ከተፈጥሮ እና ከማኅበራዊ አቅማችን ጋር የተመጣጠነ የህዝብ እድገት ለማምጣት ቁጥጥር መደረግ አለበት የሚለው የወደፊት የመድረክ አዘጋጆች አስበውበት ብንወያይ ለማለት ነው፡፡

3. እኔ በእውነቱ አቅራቢዎቹ በራሳቸው አመለካከት ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? ደሀስ ማን ነው? የሚለው የራሳቸው አመለካከት በጥሩ ሁኔታ አስቀምጠውታል፡፡ ሌላውም ደግሞ እንደዚሁ በፈለገው መልክ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ የሚያሳስበኝ ጉዳይ ግን ይሄ አይደለም፡፡ ፐርሰናሊ ብዙ አያሳስበኝም፡፡ ድህነት ማለት ምን ማለት ነው? ደሀ ማነው? እኔ ብዙ የሚያሳስበኝ ምንድነው ይህን ኮንሴፕት ፊሎሶፋይስ እያደረግን የምንፈጀው ጊዜ ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር ምንድነው አቅራቢዎቹ አቅርበውልናል፡፡ ከነዚህ አቅራቢዎች ጋር ከራሳቸው አመለካከት በመነሳት ድህነትን ገልፀውታል ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው እስኪ ከእነሱ እንኳ አመለካከት ምክንያቶቹ በቅደም ተከተል አንገብጋቢ የሚባለው ይሄ ይሄ ነው፡፡ ስብዕናን የሚጋፈጡ መጥፎ ጠላታችን በተለይ እውነት ለመናገር በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ኩሩ ህዝብ ድህነትን ሀብት አድርጎ በማንኛውም መመዘኛ ለምሳሌ ድህነትን ለመመዘን ትክክለኛ አመልካች ላይገኝ አይችል ይሆናል፡፡ ትክክለኛ አመልካች ቢገኝ እንኳ አንድን ኢትዮጵያዊ ደሀ ነህ ብንለው ደሃ አይደለሁም እኔ ጤና እስከሆንኩ ድረስ፣ ሀገር ሰላም እስከሆነ ድረስ እኔ ደሃ አይደለሁም ነው የሚለን፡፡ መመዘኛ እንኳ ቢኖር እኔ እናቴን ደሃ ነሽ ስላት እኔ ደሃ አይደለሁም እኔ ጤና እስከሆንኩ እና ሀገር ሰላም እስከሆነ ድረስ አልቀበለውም ነው የምትለኝ፡፡ የወር ገቢሽ እንኳ መቶ ብር አይሞላም፡፡ በዴፊኔሽኑ መሰረት ከዘጠና ብር በታች ከሆንሽ ደሀ ነሽ ስላት በፍፁም አይደለሁም ብላ ትከራከረኛለች፡፡ ይሄ አይደለም እኔን የሚያሳስበኝ እና ጊዜያችንን ማጥፋት ያለብን በቅደም ተከተል ምክንያቶቹን አውቀን ተረባርበን ለእውነት ለመናገር ይህንን ስብእናን የሚገፍ መጥፎ ጠላታችን እንዴት እንቀርፋለን? ስለዚህ ከአቅራቢዎቹ እስኪ ለድህነት መባባስ በቤተሰባቸው ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ያባባሰው ይህ ይህ ነው፡፡ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ይበሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ጥይታችንን የምናነጣጥረው እነሱ ላይ ነው፡፡ ምክንያቶቹን በአግባቡ ከአወቅን ጊዜያችንን እዚያ ላይ አጥፍተን ምክንያቶቹን ለመግደል መረባረብ አለብን፡፡ ከዚህ መድረክ መጠቀም ያለብን በእነሱ አመለካከት ወደፊት ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ የምናደርገው ጥረት ያለብን በቅደም ተከተል አንገብጋቢ ናቸው የምንለውን ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ እዚህ ላይ ነው ማተኮር ያለብን፡፡ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ምንድነው የከበደ ሚካኤል ጥቅስ አይነት "ራሴን ሲበላኝ ውስጥ እግሬን ቢያኩኝ ለምንም አይበጀኝ ለምንም አይጠቅመኝ"፡፡ የሚበላንን ቦታ ትተን ሌላ ጋር ነው የምናከው፣ ሌላ ቦታ ነው የምንረባረበው፡፡ መንግስታዊ የሆነም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅትም እንኳ የራሱ የሆነ ድክመት ሊኖረው ይችላል፡፡ ግን እሱም ቢሆን በአግባቡ እነዚህ ናቸው ምክንያቶቼ ይሄ ነው ፍላጎታችን በዚህ ላይ መነጋገር አለብን አብረን በጋራ መሄድ አለብን፡፡ አቅራቢዎቹ በትርጉሙ ላይ ደሃ ማለት ይሄ ነው፣ ብዙ መፅሀፍ ተፃፈ ምንም የሚጠቅም አይመስለኝም፡፡ የሚጠቅመው ከአሁን ወዲያ ትርጉም ያለውን ስራ እየሰሩ ድህነትን እዚህ ላይ ቀርፈን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያኖችን ከድህነት መስመር በላይ እንዲኖሩ አድርገናል፣ ድህነትን ቀንሰናል ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር የምንችለው ከዚህ መድረክ አንድ ልንጠቀም የሚገባን ነገር ቢኖር ይሄ መሆን አለበት ለማለት ነው፡፡

4. እኔ የዛሬዎቹን ተናጋሪዎች በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በጣምም አደንቃቸዋለሁ፡፡ በህዝብ ፊት ብዙ ጊዜ ተነግረው የማያውቁት በህዝብ ፊት ሀፍረት መስሎ የሚታየንን ሀሳብ መድረክ ላይ ወጥተው ስለራሳቸው ሲናገሩ እኔ ትልቅ አክብሮት ነው ያለኝ፡፡

እራሱ ድህነትን ዛሬ አብረን ያደግንበት እያየን በየመንገዱ በየቤታችን በየጎረቤታችን እንደ ባህል እንደ አካላችን አይተን የኖርንበትን ነገር ዛሬ እንደቁም ነገር አውርተን በመድረክ ላይ እየተነጋገርን ነው፡፡ ይኸንን ነው፡፡ ይኸንን ዕድል የሰጠን ይመስለኛል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የዓለም ባንክ በጠየቀው ጊዜ ፅፎ የሰጠውን የዓለም ባንክ ቢቀበል ኖሮ ይህንንም ዕድል አናገኘውም ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንንም እንደ ዕድል ቆጥሮ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ዕድሉን ጨብጦ ማነጋገሪያ መድረክ አድርጎ ማቅረቡ በተለያየ እስካሁን ስንነጋገርበትና ጥሩ ሀሳቦች

እየመነጨ በመፅሔት እየተፃፉ ባለቤት የሆኑትን ዛሬ መድረኩ ላይ አውጥቶ ማነጋገሩ ይኼ ትልቅ እርምጃ ነው:: ይሁን እንጂ ይሄ መነጋገር ይኼን ሀሳብ፣ ከየወገኑ የሚፈልቀውን ሀሳብ አዳማጩ ማነው? ተቀባዩ ማነው? ስራ ላይስ የሚያውለው ማነው? ዛሬ በመካከላችን የመንግስት አካላት አሉ ወይ? እነዚህ በየመድረኩ እያለቀሱ የተናገሩትን የሚያዳምጥ ቢያዳምጥም በአንድ ጊዜ ለውጥ ያመጣል ባንልም ቢያንስ አብሮ የመንግስት አካል አለ? ተወርውሮ ሲወድቅበት መልሶ የግድ ለህዝብ ማስማት ግድ የሆነበት መንግስት ተወካዮች አሉ? U.N.D.P. ተወካይ በመካከላችን እንዳሉ ሁሉ ከመንግስት አሉ ወይ? ዝም ብሎ ኤክስርሳይስ ነው ወይ? ወዴት ነው የሚሄደው? መጨረሻ የተመረጡት የተለመደው ኮሚቴዎች ዕፊው ነው የሚሰጡት:: ይሄ ሁሉ የሚፃፈው ለማን ነው? የሚደርሰው ይሄንን ይመስለኛል:: ማኅበራዊ ጥናት መድረክ ራሱ ምናልባት አስተያየት ሊሰጥበት ይችላል:: አለዚያ በየጊዜው የሚደረጉ ነገሮች ዋጋቸው ምንድነው የሚሆነው? የዛሬው መድረክ ልዩ ሆኖ ነው ያየሁት:: አመሰግናለሁ:: ምናልባት በN.G.O. ተረድተው በመፍጨርጨር ላይ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በመፍጨርጨር ሰው ለመሆን በመጣር ላይ ያሉትን እና ሰው ማለት ከችግር ለመላቀቅ ሌሎች ደግሞ ቀኑ ጨልሞባቸው በምንም ዓይነት ድሮ በነበሩበት ያሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ቢሳተፉ ኖሮ ይበልጥ ጥሩ ይሆን ነበር:: እህቴ ስትናገር በዕንባ ነበር የገለፀችው:: እኔም አንብቼያለሁ:: ይሄ ደግሞ በሷ ንግግር ሳይሆን ከእሷ ንግግር እያዛመድኩ በዛው ውስጥ የማስባቸው ብዙ ሰዎች ስላሉ ነው:: እንደሷ ካሉ ልጆች ጋር ስለምሰራ ነው:: ወደዋናው ነገር ልምጣና እነዚህ የተቸገሩ ሰዎች የሚሻሻሉበት መንገድ ምን ዓይነት ነው? የጋራ የሆነ ባህርይ አለ:: ድሆች ሰርተው ሲሻሻሉ እናያለን:: ምንም ሳይኖራቸው ያለምንም ድጋፍ ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ይኸውም ምንድነው ያ የጋራ ባህርይ ለምን ያንን የጋራ ባህርይ ሰብስበን አናሳድገውም በሚለው ላይ ለምሳሌ መቆጠብ አንዱ ነው:: እህቴ እንዳለችው እሷ ቆጥባ ለቤተሰቦቿ ለህክምና አዋለችው:: ያኛው ጓደኛዋ ግን ቆጥቦ ሰራበት:: አገኘበት:: ሌላው ጥረት ነው:: ለድህነት እኛ እራሳችን ተጠያቂ የምንሆንበት ነገር አለ:: ደሃ ለመሆኔ የእኔ አስተዋፅኦ አለ ወይ? ለድህነቴ እዚህ ላይ ይህንን ነገር አውቀን መልስ በዚያ ብንሰጥበት ትልቅ ነገር ይመስለኛል:: እያንዳንዳችን ለራሳችን ተጠያቂነት በድህነታችን ሊኖር ይችላል:: ሌሎችም ነገሮች ሁሉ ቢኖሩም ለማለት ነው:: ያንን ነገር በጋራ የምንወጣበት መንገድ ከ206 ሀገሮች 206ኛ ወጥታለች የሚል ኢንፎርሜሽን በዛሬው ዕለት በዚህ ወር በወጣ ጆርናል አይቻለሁ:: ከዚህ እንዴት ነው የምንወጣው? ሌላው ልናገር የምፈልገው ስለ ትርጉሙ ነው:: ድህነትን ስለመወሰን እኔ የሚቻል አይመስለኝም:: በጣም ቀላል እንደሆነ እዛ ጋር ሲነገር አሁን ሰምቻለሁ:: በምንም ዓይነት ልጅቷንም ሆኜ እኔ ድህነትን ላውቀው አልቻልኩም:: በምንም ዓይነት ድህነት ይህ ነው ሊባል አይችልም:: ድህነት አያናግርምም:: ድህነት በአንድ ነገር ብቻ ሊገለጥ ይችላል ይኸውም በለቅሶ:: ይህንን በስራ ያየሁት ነው:: ድህነት በዚህ አንፃር ብናየው ጥሩ ይመስለኛል አመሰግናለሁ::

*<u>ከማጥመ የተሰጠ ማሳሰቢያ</u>*

ከዚህ መድረክ ስለ ፕሮግራሙ የተሰነዘሩት ጥያቄዎች ስላሉ በአንዱ ማብራሪያ ልስጥ ብዬ ነው:: ከእዚህ ከወንድሜ ከማኅበራዊ ጥናት መድረክ በድህነት ላይ ጥናት ቢያደርግ ጠለቅ ያለ ምርምር ቢያደርግ በተለይ ድህነት ስፋትና መጠኑ ምን ያክላል? በሀገራችን መመዘኛዎቹስ ምንድን ናቸው? ደሃ የሚባለው የኅብረተሰብ ክፍላችንስ ከድህነት ጋር የሚያደርገው ውጊያ Coping Strategy ምን ይመስላል? የሚደረገው ጥናት በተለይ እኔ እንደገባኝ ድህነትን ለመቅረፍ Appropriate Intervention Strategy እንዲረዳ ቢሆን ጥሩ ነው ብሎ አስተያየት ሰጥቶ ነበር:: እቀበለዋለሁ:: ሌሎቹም ተሳታፊዎች ተመሳሳይ ሀሳብ ሰንዝረዋል:: በዚህ አጋጣሚ ለመናገር የምፈልገው ይሄ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ Poverty Dialoge Programme ሁለት አካል አለው:: አንደኛው የተለያዩ የኅብረተሰብ አካላትን ለምሳሌ ዛሬ ከደሃው የኅብረተሰባችን ወገን ተወክሎ የመጡትን በውይይት የሚያሳትፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው በጥናትና በምርምር ላይ ተመርኩዞ ድህነት በሀገራችን ምን ይመስላል? መጠኑስ? ስፋቱስ? በገጠርና በከተማ ገፅታዎቹስ ምን ይመስላሉ? ማኅበራዊ ገፅታዎቹስ? ኢኮኖሚያዊ ገፅታዎቹስ: ፆታዊ ገፅታዎች (Gender Dimension)? የሚለው ይሄን ያካተተ ሁለተኛ ክፍል የጥናትና የምርምር ፕሮግራም አለው:: እናም ብዙዎቹ ተሳታፊዎች እንዳነሱት ይሄን ያጠቃልላል:: በጥናቱና በምርምሩ ሌላው ለማንሳት የምፈልገው ምንድነው አሁን የተሰነዘረ አስተያየት አለ:: እንዲያውም ይሄ የሚደረገው ውይይት ባክኖ ነው ወይ የሚቀረው? ወይስ መንግስት ጆሮ ይደርሳል? ወይስ የሚመለከታቸው አካላት ውይይቱን ወይም ጥናቱን ያገኙታል ወይ? እንደዚህ ዓይነት ውይይት በምናደርግበት ጊዜ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነው የምንጋብዘው:: አንድም በየጊዜው የመንግስት ተወካዮችን እንጋብዛለን::

የመንግስት ፖሊሲ በድህነት አንፃር ማብራሪያ እንዲሰጡን እንጋብዛለን፡፡ እሱን በተመለከተ በሚቀጥለው ውይይት በምናደርገውና መንግስትና የዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች በሚያደርጉት የውይይት መድረክ የሚታይ ሲሆን፣ እነዚህ ያነሳችኋቸው ባአጠቃላይ ለማለት የምፈልገው እዚህ የተነሱት አስተሳሰቦች Concerns ለእኔ Legitimate ናቸው፡፡ እናም We are taking care of them. አመሰግናለሁ፡፡

5. የድህነት መንስኤ ብዬ የማስበው መጀመሪያ ቤተሰቦቻችን መጥነው አይወልዱም፡፡ ኑሯቸውን ሳያውቁ በ100 ብር ገቢ 6 ልጅ ይወልዳሉ፡፡ ማስተዳደር ያቅታቸዋል፡፡ ስለዚህ የድህነት መንስኤ አንድም የቤተሰቦቻችን መጥኖ አለመውለድ ይመስለኛል፡፡ መፍትሄ ብዬ የማስበው ከአሁን በኋላ ላለው ትውልድ፣

   (ሀ) መጥኖ እንዲወልድ
   (ለ) መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጀመሩት መንገድ የተቻላቸውን ያህል ደሀውን ፈልገው ቢረዱና በተቻላቸው መጠን ቢያስተምሯቸው፣ ስራም በመቅጠር ትንሽም ቢሆን ኑሯቸው ይሻሻላል፡፡

   በአንድ ወቅት ስራ ተገኝቶልኝ ስራ ልገባ ሄጄ አለባበሴን አይተው ስራ እንደከለከሉኝ ነው የምነግራችሁ፡፡ እናም በልብስ እናምናለን፡፡ መስራት እየፈለገ ከአቋሙ ገና ለገና ሲገባ የሆነ ነገር ያደርገኛል የሚል አመለካከት አለው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደሀውን አይቶ ቢቀጥር የእዚያ የደሃ ቤተሰብ ልጅ ስራ ከገባ የቤተሰቡን ችግር ትንሽ ስለሚቀርፍ ከድህነት ይላቀቃል ብዬ አስባለሁ፡፡ ብዙ ደሃዎች አሉ፡፡ እቤት ውስጥ አንድ ስራ የሌለው፡፡ አሁን እኛ ቤት ውስጥ ስምንት ነን፡፡ ስምንታችንም ስራ የለንም፡፡ አባቴ ጡረታ ወጥቷል፡፡ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ፡፡ ይሄ ድርጅት አግኝቶኝ መዝገቦ የሚያስተምረኝ እንጂ በራሴ ጥረት ነው በየሰዉ ቤት ልብስ እማጥበው እኔ ግን ስራ ቢኖረኝ ታናናሾቼን አስተምራቸዋለሁ፡፡ በተኛለኝ አቅም እሰራለሁ፡፡ ትንሽም ቢሆን ከችግራችን እንላቀቃለን ብዬ አስባለሁ፡፡ ከአንድ የደሀ ቤተሰብ ውስጥ አንዱ ስራ ቢያገኝ ትንሽም ቢሆን ከድህነት ይላቀቃል ብዬ አስባለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

6. የድህነት መንስኤው ምንድነው የሚሉት ለእኔ በሁለት በኩል ላየው እችላለሁ፡፡ የውርስ ድህነት ሊኖር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከአነስተኛ ቤተሰብ ወይም ደሃ ከሆነ ቤተሰብ በመወለድ፡፡ እስከመጨረሻው ደሃ ሆኖ ሕይወቱን የሚያሳልፍ ሊኖር ይችላል፡፡ ሌላው ደግሞ ከግዜ በኋላ በእቅድ ባለመኖር በእቅድ የኑሮ ሁኔታ አለመመቻቸት፣ በዕቅድ ባለመውለድ ምክንያት ኖሮት ሊያጣ ይችላል፡፡ ይህ ለስህተት ምክንያት ነው፡፡ በዕቅድ ካልተመራ ወደድህነቱ ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለመፍትሄው ይሄን ያህል ከተነጋገርን መፍትሄው ግን ምን ሊሆን ይችላል? የሚባለው ነገር ችግሩ ከመጣ በኋላ ችግሩን በፀጋ መቀበል ነው፡፡ በመትጋት መቀበል ነው፡፡ በምን መጣ? ለምን መጣ? እንዴት እኔን ሊደፍር ቻለ? ካለንበት ቦታ የምንሸሽ እጅ የምንሰጥ ከሆነ ይሄ ድህነት ሊለቀን አይችልም ማለት ነው፡፡ ግን በፀጋ ተቀብሎ አነስተኛ ስራ ባለመናቅ ለምሳሌ ከእኔ መጀመር እችላለሁ ይሄንን ነገር በአነስተኛ ክፍያ ስራ ብባል አይ እንዴት ይሆናል አልሰራም ልል እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ባህር ማዶ ሄጄ ከዚህ የባሰ ስራ እየሰራሁ መከራና ችግር ሲፈራረቅብኝ ይታያል፡፡ በዚህ ባበቃ ይሻላል፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

# FSS Publications List

***NOTE:*** All FSS publications (except **MEDREK**) are distributed by Image International, a local book agent. Its address is P.O.Box 80766, Addis Ababa; tel. 251-1 51 09 54; e-mail: image@telecom.net.et

**FSS Newsletter**

*Medrek* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

**FSS Discussion Papers**

No. 1. *Water Resource Development in Ethiopia: Issues of Sustainability and Participation.* Dessalegn Rahmato. June 1999

No. 2. *The City of Addis Ababa: Policy Options for the Governance and Management of a City with Multiple Identity.* Meheret Ayenew. December 1999

No. 3. *Listening to the Poor: A Study Based on Selected Rural and Urban Sites in Ethiopia.* Aklilu Kidanu and Dessalegn Rahmato. May 2000

No. 4. *Small-Scale Irrigation and Household Food Security. A Case Study from Central Ethiopia.* Fuad Adem. February 2001

No. 5. *Environmental Impact of Development Policies in Peripheral Areas: The Case of Metekel, Northwest Ethiopia.* Woldeselassie Abbute. Forthcoming, 2001

No. 6. *The Environmental Impact of Small-Scale Irrigation: A Case Study.* Fuad Adem. Forthcoming, 2001

No. 7. *Land Redistribution and Women's Land Rights.* Yigremew Adal. September 2001

**FSS Monograph Series**

No. 1. *Survey of the Private Press in Ethiopia: 1991-1999.* Shimelis Bonsa. 2000

No. 2. *Environmental Change and State Policy in Ethiopia: Lessons from Past Experience.* Dessalegn Rahmato. 2001

**FSS Conference Proceedings**

1. *Issues in Rural Development. Proceedings of the Inaugural Workshop of the Forum of Social Studies, 18 September 1998.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000
2. *Development and Public Access to Information in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000
3. *Environment and Development in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2001
4. *Food Security and Sustainable Livelihoods in Ethiopia.* Edited by Yared Amare. 2001
5. *Natural Resource Management in Ethiopia.* Edited by Alula Pankhurst. 2001

*(Continued on next page )*

*(Continued from previous page )*

**Consultation Papers on Poverty (series)**

No. 1. *The Social Dimensions of Poverty*. Papers by Minas Hiruy, Abebe Kebede, and Zenebework Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. June 2001

No. 2. *NGOs and Poverty Reduction.* Papers by Fassil W.Mariam, Abowork Haile, Berhanu Geleto, and Jemal Ahmed. Edited by Meheret Ayenew. July 2001

No. 3 *Civil Society Groups and Poverty Reduction.* Papers by Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. August 2001.

No. 4 *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse. In Amharic. Edited by Meheret Ayenew. October 2001.

**Books**

1. *The View from Below: Democratization and Governance in Ethiopia.* Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Forthcoming (Co-published by FSS)

**Special Publications**

*Thematic Briefings on Natural Resource Management, Enlarged Edition.* Edited by Alula Pankhurst. Produced jointly by the Forum for Social Studies and the University of Sussex. January 2001

## Forum for Social Studies

The Forum for Social Studies (FSS) is an independent, non-profit institution engaged in policy-oriented research on the development challenges facing Ethiopia. It provides an open forum for the discussion of public policy and promotes public awareness. FSS believes that encouraging broad participation in policy debates is an important contribution to the democratic process. To achieve its goals, FSS organizes public conferences, and publishes and distributes its research findings to policy makers and other government officials, civil society institutions, professionals, the business community, donor agencies and the public at large. This publication is meant to encourage public discussion of the issues concerned and their policy implications.

## Consultation Papers on Poverty

These publications are based on papers presented and discussions held at FSS' Poverty Dialogue Forum and are meant to stimulate debate and reflection on the Government's poverty initiatives.

## Address

Forum for Social Studies
P.O.Box 3089
Addis Ababa, Ethiopia

Tel. (251-1) 55 61 21/12 95 79/55 20 25
E-mail: fss@telecom.net.et

**Financial support for the Policy Dialogue Forum and this publication was provided by the FRIEDRICH EBERT STIFTUNG to which we are grateful.**

**We also wish to thank the Royal Netherlands Embassy for its generous financial assistance to FSS.**

Layout by *Mihret Demissew*